አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድኅረምረቃ መርሐግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

# በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ የኮሌጅ አማርኛ (Amha-101) የርቀት ትምህርት ሞጁዩል የቅርጽና የይዘት አደረጃጀት

ዕዝራ አየለ

ሰኔ/2000 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ
# ማሠልጠኛ የኮሌጅ አማርኛ (Amha-101)
# የርቀት ትምህርት ሞጁዩል
# የቅርጽና የይዘት አደረጃጀት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም. ኤ. ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ... LIBRARY

ዕዝራ አየለ
ሰኔ/2000 ዓ.ም

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ የኮሌጅ አማርኛ (Amha-101) የርቀት ትምህርት ሞጁዩል የቅርጽና የይዘት አደረጃጀት

በ

ዕዝራ አየለ

ቋንቋ ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

በመጀመሪያ የዚህን ጥናት ረቂቅ ያስመሰልቸት በማንበብ አስፈላጊውን እርማት እና ምክር በመስጠት እስከመጨረሻውሙያዊ ድጋፋቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶ/ር አረጋ ኃይለሚካኤል ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ መረጃዎቹን ለማሰባሰብ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ላደረገልኝ ትብብር ምሥጋናዬ ከፍተኛ ነው ፡፡

በመጨረሻም ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ በማዘጋጅበት ጊዜ የማቴሪያል እና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ላበረታቱኝ ለባለቤቴ ለወ/ሮ ሂሩት ዘውዴ እና ለልጄ ሕፃን ቤቴል ዕዝራ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## ማውጫ

ርዕስ | ገጽ


ምስጋና ... i
የይዘት ማውጫ ... ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ... iv
የአባሪ ዝርዝር ... v
አጠቃሎ ... vi
ክፍል አንድ ... 1
መግቢያ ... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ... 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ ... 3
1.3. የጥናቱ ክልልና ገደብ ... 4
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ... 4
1.5. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ... 5
ክፍል ሁለት ... 7
ክለሳ ድርሳን ... 7
2.1 የርቀት ትምህርት ምንነት? ... 7
2.2 የርቀት ትምህርት ተማሪ ባሕርይ ... 10
2.3 የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ባሕርይ ... 10
2.4 የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት ሂደት ... 12
2.4.1 የኮርስ ዕቅድ ... 12
2.4.2 የኮርስ ዝግጅት ... 13
2.5 የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ግምገማ ... 14
2.5.1 የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ክለሳ ... 15
2.5.2. የርቀት ትምህርት ሞጁዩል መገምገሚያ ከቅርጽና ከይዘት አደረጃጀት አንጻር ... 16
2.6 ለመደበኛው ትምህርት የሚዘጋጁ መጻሕፍትና ለርቀት ትምህርት የሚዘጋጁ መጻሕፍት ንጽጽር ... 18
2.7 በቋንቋ ትምህርት ዝግጅት የሚቀረጹ ዓላማዎችንና ይዘቶች ዝምድና ... 20
ክፍል ሦስት ... 21
የአጠናን ዘዴ ... 21

3.1 የጥናቱ ዘዴ ..... 21

3.2 የመረጃ ምንጮች ..... 22

3.3. የናሙና አመራረጥ

3.3.1. የኮሌጅ አማርኛ /Amha-101/ የርቀት ሞጅዩል ናሙና ..... 22

3.3.2. የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ ..... 22

3.3.3. የሞጁዩል አዘጋጆች እና የርቀት መርሐግብር አስተባባሪዎች ናሙና አወሳሰድ ..... 22

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ..... 23

3.4.1 የሰነድ ትንተና ..... 23

3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ ..... 23

3.5 የአተናተን ዘዴ ..... 23

ክፍል አራት ..... 24

የመረጃ ትንተና ..... 24

4.1 የሰነድ ትንተና ውጤት ..... 24

4.1.1 የሞጅዩሉ ቅርጽ ..... 24

4.1.2 የሞጁዩሉ የይዘት አደረጃጀት ..... 25

4.1.2.1 መክፈቻ /Opening Section/ ..... 25

4.1.2.2. ዋና አካል ..... 34

4.1.2.3 መዝጊያ (Ending Section) ..... 37

4.2. ከርቀት ተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተናና ትርጉም ..... 37

4.2.1. የሞጅዩሉ ቅርጽ ..... 37

4.2.2 የሞጁዩሉ የይዘት አደረጃጀት ..... 39

4.3 ከሞጁል አዘጋጆች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ..... 44

4.4 ከርቀት ትምህርት ክፍል የተሰበሰበ መረጃ ..... 45

4.5 የተሰበሰቡ መረጃዎች ተዛምዶ ..... 46

ክፍል አምስት ..... 47

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች ..... 47

5.1 ማጠቃለያ ..... 47

5.2 የመፍትሔ ሃሳቦች ..... 49

ዋቢ ጽሑፎች ..... 51


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# የሠንጠረዥ ማውጫ


ገጽ

ሠንጠረዥ አንድ፦ የክፍል አንድ ዓላማዎች ዋና ዋና ይዘቶች ............................ 26

ሠንጠረዥ ሁለት፦ የክፍል ሁለት ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች ..........................27

ሠንጠረዥ ሦስት፦ የክፍል ሦስት ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች ......................... 28

ሠንጠረዥ አራት፦ የክፍል አራት ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች ......................... 29

ሠንጠረዥ አምስት፦ የክፍል አምስት ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች..................... 29

ሠንጠረዥ ስድስት፦ የክፍል አንድ ዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች ............... 30

ሠንጠረዥ ሰባት፦ የክፍል ሁለት ዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልምጃዎች ................. 31

ሠንጠረዥ ስምንት፦ የክፍል ሦስት ዓላማዎች፣ ተግባሮች እና መልመጃዎች ........... 32

ሠንጠረዥ ዘጠኝ፦ የክፍል አራት ዓላማዎች፣ ተግባሮች እና መልመጃዎች ............... 33

ሠንጠረዥ አሥር፦ የክፍል አምስት ዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች ............... 33

ሠንጠረዥ አሥራ አንድ፦ በ2000 ዓ.ም በመማር ላይ ካሉና ከቀድሞ ተማሪዎች
የሞጅዩሉን ትርጉ በሚመለከት የተሰበሰበ መረጃ............... 38

ሠንጠረዥ አሥራ ሁለት፦ በየይዘቱ የተካተቱ ዓላማዎችን በሚመለከት የተሰበሰበ መረጃ. 39

ሠንጠረዥ አሥራ ሦስት፦ በየምዕራፉ ስለ ይዘቶች የተሰበሰበ መረጃ ........................ 40

ሠንጠረዥ አስራ አራት፣ ‐ ተግባሮችንና መልመጃዎችን በሚመለከት የተሰበሰበ መረጃ ... 41

ሠንጠረዥ አሥራ አምስት፣ የይዘቶች ደረጃ መለያ ............................................. 43

ሠንጠረዥ አሥራ ስድስት፦ ሞጁዩል አዘጋጆች በርቀት ትምህርት ላይ የወሰዱት ሥልጠና.44


UNIVERSITY LIBRARY

# የአባሪዎች ዝርዝር


**የአባሪዎች መለያ** **ገጽ**

አባሪ አንድ: በኮሌጅ አማርኛ ውስጥ ያሉ ምልክቶች መፍቻ ........................... 54

አባሪ ሁለት: የሞጁዩሉ ውስጣዊ ይዘት አጻጻፍ ለናሙና የቀረበ ገጽ ................. 55

አባሪ ሦስት: መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ........................................ 61

3.1. የሰነድ መፈተሻ መስፈርት /ቅጽ 1/ ........................................ 61

3.2. ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ /ቅጽ 2/ ..................... 64

3.3. ለአዘጋጆች የተሰጠ የጽሑፍ መጠይቅ /ቅጽ 3/ ........................ 68

3.4. ለአስተባባሪዎች የተዘጋጀ የቃለ መጠይቅ መሪ

ጥያቄዎች (Questionnaire Guide) .................................... 70

# አጠቃሎ (Abstract)

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ አማርኛ (Amha- 101) ከርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት አንጻር ጥናቱ ያተኮረባቸውን የሞጁዩሉ ክፍሎች መፈተሸ ነው፡፡ ጥናቱ በተጨማሪም ለሚገኙት ችግሮች መፍትሔ ሐሳቦችን በመጠቆም ትምህርቱ ውጤታማና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው የአጠናን ስልት የአይነታዊ ምርምር ዘዴ አካል የሆነውን ገላጭ ጥናት ነው፡፡ ለጥናቱ ማግኚያ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሠነድ ፍተሻ፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ የጥናቱ መጠነ ርዕይ ቅርጹን በሚመለከት፤ ዕይታን መሳብ፣ የፊደሎች መጠን ፤ መልስ ለመስጠትም ሆነ ማስታወሻ ለመያዝ በቂ ቦታዎች መኖራቸው፤ መመሪያና ምልክቶች አመላካች መሆናቸውን መፈተሸ ነው፡፡ በተጨማሪም የይዘት አደረጃጀትን በሚመለከት፤ በግልጽ ቋንቋ መቅረቡ፣ በቂ መሆኑ፣ ከዓላማና ከተግባሮችጋር መጣጣሙ፣ ተግባሮችና መልመጃዎች በበቂ ሁኔታ በአጭር ርቀት መደረጃታቸውና ተገቢ ማመሳከሪያዎች መኖራቸው የሚሉ ነጥቦች ላይ ነው፡፡ ኮሌጅ አማርኛ (Amha- 101) ፤100 የ2000 ዓ.ም ተማሪዎች፣ 40 የቀድሞ ተማሪዎች፣ 7 መምህራንና 1 የርቀት ትምህርት አስተባባሪ በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ በተሰበሰበው መረጃ በተገኘው ውጤት ጥናቱ ያነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች አዎንታዊም አሉታዊም ምላሽ አግኝተዋል፡፡ የሞጁዩሉ አዘገጃጀት በአዘብዛኛው የርቀት መማሪያ አዘገጃጀትን ስልት የተከተለ ነው ፡፡ በተጨማሪ ዓላማዎች ግልጽና አመላካች ናቸው፡፡ ከይዘቶችና ተግባሮች ጋር ይዛመዳሉ፤ መመሪያዎችና ምልክቶች አመላካች ናቸው፡፡ መልመጃዎችና ተግባሮች በበቂ ሁኔታና በአጭር ርቀት የተደራጁ ናቸው ፡፡ በተጨማሪም ተግባሮች ተገቢ ማመሳከሪያ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ይዘቶች ግልጽነት የጎደላቸውና ተጨማሪ ማብራሪያ የሚፈልጉ ሆነው ተገኝተዋል ፡፡ የቀድሞው ሞጂዩል የፊደሎች መጠን አናሳ መሆኑና ለንባብ አመቺ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በሞጁዩሉ በደካማ ጎን የተጠቆሙ ጉዳዮችን የማስተካከል እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለአዘጋጆች የርቀት ትምህርት ስልጠና እንዲሰጥ ወይም የርቀት ሞጁዩል ዝግጅት የመስኩ ባለሙያዎችን ቢያካትት፣ የተጠናከረ መረጃ ሊያስገኝ የሚችል ጥናት እንዲደረግ የሚሉ ዋና ዋና የመፍትሔ ሐሳቦች ተጠቁመዋል፡፡


ABABA UNIVERSITY
LIBRARY

# ክፍል አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ዛሬ በዓለማችን የሰው ልጅ አካባቢውን ለኑሮው እንደሚስማማው ለመለወጥ፣ እንዲሁም ራሱን በየጊዜው ከሚለማዋወጠውና ከሚያድገው አካባቢው ጋር እያጣጣመ መኖር የሚያስችለውን የዕውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት መዳበር ትምህርት ለማግኘት፣ የተለያዩ አማራጮችን ይፈልጋል። ይህንን ፍላጎቱን ለማርካት በመደበኛው የትምህርት ሥርዓት የማያልፍባቸው ሁኔታዎች ብዙ ናቸው። ለምሳሌ፦ የሥራ ባሕርይ፣የቦታ ርቀት፣የአካል ጉዳት ወዘተ. የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህንና የመሳሰሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ አገሮች የትምህርት መርሐግብራቸውን በመደበኛ የትምህርት መርሐግብር ብቻ እንዲሆን አልወሰኑም፤ የርቀት ትምህርትን መርሐግብር ተግባራዊ በማድረግ የትምህርትን ሥርጭት እያስፋፉ ይገኛሉ።

ይህንን አስመልክቶ Ejeta (2005:13) ያደጉ አገሮች የርቀት ትምህርትን ጠቀሜታ በመገንዘብ፣ በስፋት ተግባራዊ እያደረጉ እንደሚገኙና ሌሎችም በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ፈለጋቸውን በመከተል ትምህርትን ለማስፋፋት እንደ አማራጭ መውሰዳቸውን ያስረዳሉ፤ እኚሁ ሰው በዚሁ ገጽ የUNESCO (2000) ሪፖርት በመጥቀስ፣

- በአውሮፓ፦ እንግሊዝ፣ እስፔንና ፈረንሳይ
- በደቡብ አሜሪካ ፦ ዑራጓይና አርጀንቲና
- በኢሲያ፦ ህንድ፣ማሌዥያና ፖኪስታን
- በአፍሪካ፦ ኬኒያና ታንዛኒያ

የርቀት ትምህርትን ለተለያዩ የትምህርት መስኮች ሥርጭት እንደሚጠቀሙበት ያስረዳሉ።

በአገራችንም በ1960ዓ.ም. በቀለም ትምህርት ደረጃቸው ዝቅ ያሉና በመምህርነት ሙያ የሠለጠኑ መምህራንን በሥራ ላይ ሥልጠና የቀለም ትምህርት ብቃታቸውን ከፍ ለማድረግ "ዳይሬክትድ ስተዲ ፎር ቲቸርስ" የሚባል መርሐግብር በርቀት ትምህርት መልክ እንደተጀመረ፣ በዚህም መርሐግብር በራሳቸው ሊያስተምሩ የሚችሉ እትሞች፣ መልመጃዎች፣የማረሚያ መልሶችና የጥናት መመሪያዎች ከመደበኛው የመማሪያ መጽሐፍት ጋር ተቀናጅተው ይሠራባቸው እንደነበር እነ ጌታቸው (1983 ፡ 28) ያስረዳሉ።



ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

የመምህራንን የሙያ ክህሎትና ዕውቀት በርቀት ትምህርት መርሐግብር ወደ ዲፕሎማ ደረጃ ለማሳደግና በሁለተኛ እርከን (ከ5 - 8) የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶችን አቅም በሰው ሀይል ለማሟላት ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ የትምህርት ሚኒስተር ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር በመተባበር ሲሰራ ቆይቷል።

የደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅም የዲፕሎማ መርሐግብር በመክፈት ቀደም ሲል በሠርተፊኬት ደረጃ ሠልጥነው በሥራ ላይ የሚገኙ መምህራንን ከ1998ዓ.ም. ጀምሮ በርቀት መርሐግብር በማሥተማር ላይ ይገኛል።ይሁንና በዚህ ሂደት የአጠቃላይ መርሓግብሩም ይሁን የመርሓግብሩ ልዩ ልዩ ግብዓቶች ጠንካራና ደካማ ጎን ላይ የተደረገ ጥናት የለም።

በርቀት መርሐግብር ከሚመደቡት ግብዓቶች ውስጥ የመማሪያ ሞጁዩሎች የሚጠቀሱ ናቸው። በኮሌጁ ተዘጋጅቶ ከ1998ዓ.ም. ጀምሮ ለርቀት ተማሪዎች በማገልገል ላይ ያለውም ኮሌጅ አማርኛ /Amha-101/ ላይ እስካሁን የተደረገ ጥናት የለም።

በርቀት ትምህርት ሂደት በመምህራንና በተማሪዎች (በትምህርት ሰጪው ድርጅትና በትምህርት ተቀባይ አካል) መካከል ግንኙነት የሚመሠረተው በዋናነት በተለያዩ የሕትመት ውጤቶችና የድምጽ መማሪያዎች አማካይነት ነው፤ እነዚህ የትምህርት ሚዲያዎች ምንም እንኳን በተለያዩ የቁጥጥር ደረጃዎች አልፈው ተማሪው የሚገለገልባቸው ቢሆንም የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ እና ውጤታማ ለመሆን በተለያየ ጊዜ ሊገመገሙ ይገባል። ለዚህም ተግባር የሂደት ግምገማና ማጠቃለያ ግምገማ ማድረግ ተገቢ መሆኑን Woodley እና Adrian (1988: 291-98) ያስረዳሉ።

በመሆኑም አጥኚው ለዚህ አጭር ጥናት ያነሳሳው ጉዳይ፣

- ጥናቱ ያተኮረበት የደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅም፣ የርቀት ትምህርት መርሐግብር በክልሉ ትዕዛዝ መሠረት ቀደም ሲል ለመደበኛ ተማሪዎች የተዘጋጁትን ሞጁዩሎች ለርቀት ትምህርት በሚያመች መልኩ አሻሽሎ እየተጠቀመበት በመሆኑ እና ለዚህም ወቅታዊ ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አጥኚው በማመኑ፣
- አጥኚው በዚሁ ኮሌጅ በሥራ ላይ በቆየበት ጊዜ የርቀት ሞጁዩሎች በአብዛኛው የሚዘጋጁት የርቀት ሞጁዩል አዘገጃጀት ሥልጠና ባልወሰዱ ወይም ልምዱ በሌላቸው መምህራን መሆኑን በመታዘቡ፣

- አጥኚው በመስኩ በተከታተለው የድሕረ ምረቃ መርሐግብር የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ከመደበኛ ተማሪዎች መጽሐፍ በተለየ የራሱ ያዘገጃጀት ሥርዓት እንዳለው ስለተገነዘበና ይህንንም መነሻ በማድረግ ባደረገው የቅኝት ጥናት ሳቢያ ከተማሪዎች ባገኘው መጋቢ ምላሽ የተነሳ፣የአንድ መርሐግብር ውጤታማነት በአተገባበሩ መሠረት የሚመዘን በመሆኑና ለርቀት መርሐግብር የተዘጋጁ የቋንቋ ሞጁዩሎችም መጠናት እንዳለባቸው የሚያምን በመሆኑ የሚሉት ናቸው፡፡

ከርቀት ትምህርት ባሕርያት አንጻር፣ ለተማሪዎች የሚዘጋጁ የመማሪያ ሞጁዩሎች ትኩረት እንደሚገባቸው የዘርፉ ምሁራን በጥናቶቻቸው ጠቁመዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Melton (2002:5) እና Judith (1994:86)፣ የርቀት ትምህርት አንዱ ትኩረት የርቀት መማሪያ ማዘጋጀት ነው፤ በመሆኑም ለርቀት ትምህርት ተብለው የሚዘጋጁ ሞጁዩሎች በየጊዜው ሊፈተሹ፣ ሊስተካከሉና ሊከለሱ ይገባል፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ ለርቀት ትምህርት መርሐግብር የተዘጋጀውን ኮሌጅ አማርኛ /Ama-101/ ከርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት አንጻር የቅርጽና የይዘት አደረጃጀቱን መፈተሽና ለሚገኙት ችግሮች መፍትሔ ሐሳቦችን በመጠቆም ትምህርቱ ውጤታማና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በዚህም አጠቃላይ ዓላማ ሥርም ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፤

ሀ. በርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት መሠረት የኮሌጅ አማርኛን የቅርጽና የይዘት አደረጃጀት ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት ለማሳየት፣

ለ. ኮሌጅ አማርኛን ለማሻሻል ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በጥናቱ የተደረሰባቸውን ክፍሎች ለመለየትና ለማሳየት፣

ሐ. ኮሌጅ አማርኛን ለማሻሻል የሚረዱ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለመጠቆም፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከነዚህ ዝርዝር ዓላማዎችም በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሂደቱ ይመልሳል፤

1. በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ ለርቀት ትምህርት መርሐግብር የተዘጋጀው ኮሌጅ አማርኛ /Amha-101/ ምን ያህል የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት ስልትን የተከተለ ነው?

2. በሞጁዩሉ የሚማሩት የርቀት ትምህርት ተማሪዎች የሚቸገሩባቸው የሞጁዩሉ ክፍሎች አሉን? ካሉስ የትኞቹ ናቸው?

3. ኮሌጅ አማርኛ ከርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት አንጻር ቅርጽና ይዘቱ ሲቃኝ ምን ምን ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት?

## 1.3. የጥናቱ ክልልና ገደብ

ይህ ጥናት በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ በተዘጋጀው ኮሌጅ አማርኛ ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው። ሌሎች ለርቀት መርሐግብር የተዘጋጁ ሞጁዩሎችን አይመለከትም።ስለሆነም በ1999ና 2000 ዓ.ም. ይህንን ኮርስ በርቀት ትምህርትነት በወሰዱና እየወሰዱ ያሉ ተማሪዎችን በተሳታፊነት ያካትታል።

ከይዘት አንጻርም ጥናቱ የሚያተኩረው ከርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት አኳያ ውስጣዊ የይዘት አደረጃጀቱንና ቅርጻዊ ተገቢነቱን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን የተወሰኑ ክፍሎቹን ይመለከታል። በቅርጽ ሥርም እይታን መሳብ፣ የፊደሎች መጠን፣ መልስ ለመስጠትም ሆነ ማስታወሻ ለመያዝ በቂ ቦታ መኖር፣ የምልክቶችና መመሪያዎች ግልጽነት ይካተታሉ። እንዲሁም በይዘት አደረጃጀት ሥር ግልጽ፣ በቂ፣ ያልታጨቁ፣ ተግባሮች እና የግምገማ ጥያቄዎች ባጭር ርቀት የተደራጁ፣ ተገቢ ማመሳከሪያዎች፣ ከዓላማ ጋር መጣጣምን ይመለከታል።

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ተካሂዶ ሲጠናቀቅ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፤

- ለርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘጋጆች ስለ ርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት መነሻ ሀሳብ ይሰጣል፤
- ኮርሱን የሚወስዱት የርቀት ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የተዘጋጀ ሞጁዩል እንዲያገኙ አስተዋጽዖ ያደርጋል፤

- ኮሌጅ አማርኛን ለማሻሻል የሚረዱ የመፍትሔ ሐሳቦችን ይጠቁማል፤
- ክልሉ የተሻሉ የርቀት ትምህርት ሞጁዩሎችን ለማዘጋጀት የሚችሉ መምህራንን ለማስልጠን ትኩረት ይሰጣል፤
- ወደፊት በርቀት ትምህርት መስክ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኚዎች መነሻ ይሆናል፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 1.5. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ

መልመጃ = በአንድ ይዘት ላይ ማብራሪያ ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎች ከቀደመ ዕውቀታቸው በመነሳት እንዲሞክሩት የቀረበ ጥያቄ ነው። የመልመጃ ጥያቄዎች ምላሽ ከቀጣዩ ማብራሪያ ውስጥ ይገኛል።

ሞጁዩል(Module) = ተያያዥነት ያላቸውና የተመረጡ የትምህርት ይዘቶች በግል እያነበቡ ለመማር አመች በሆነ መንገድ ተደራጅተው የሚቀርቡበት የመማሪያ መማሪያ ነው። እያንዳንዱ የአንድ ሞጁዩል ይዘት መግቢያ፣ ዓላማዎችን፣ በመጠኑ የተደራጁና በልዩ ልዩ መግለጫዎች የተብራሩ ይዘቶችን፣ በየቅርብ ርቀት የተደራጁ ተግባሮችና መልመጃዎችን፣ የራስመገምገሚያ ጥያቄዎችን እንዲሁም ማጠቃለያ በዋናነት ያካትታል።

ተግባር = በየይዘቱ ጣልቃ የተደራጁ የተለያዩ ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች ሠፋ ያለ ማብራሪያ የሚፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ። በመሆኑም የማመሳከሪያ ምላሽ በሞጁዩሉ መጨረሻ ላይ አላቸው። ተማሪዎቹ የራሳቸውን ምላሽ ከሰጡ በኋላ ማመሳከሪያዎቹን በማንበብ ግንዛቤያቸውን ያዳብራሉ።

የተልዕኮ ትምህርት = በመምህርና በተማሪ መካከል ተከታታይነት ያለው የረዥም ጊዜ የፊት ለፊት ግንኙነት ሳይኖር ትምህርት በፖስታ መላላክ የሚሰጥበት ሂደት ነው። በዚህ የትምህርት ሂደት ዋና መማሪያ የሆነው ሕትመት (Print Medium) ለመደበኛ ተማሪዎች የሚዘጋጀው ነው።

የርቀት ትምህርት= በመምህርና በተማሪ መካከል የታቀደ የፊት ለፊት ግንኙነትና በተለያዩ የመማር ማስተማር ሚዲያዎች በመደገፍ ትምህርት በመላላክ የሚሰጥበት ሂደት ነው። በዚህ የትምህርት ሂደት ዋናው መማሪያ የሆነው ሕትመት (Print Medium) ከመደበኛው በተለየ መንገድ የሚዘጋጅ ነው፤ የርቀት ተማሪዎችን ባሕርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጅ ነው ። በመሆኑም በተልዕኮ ትምህርትና በርቀት ትምህርት መካከል የስርዓተ ትምህርትና የማስተማር ዘዴ ልዩነት የጎላ ነው ።

ገባ - ወጣ - ገባ (In-out-In) = በአሁኑ ጊዜ እየተሰራበት ያለ በ10+3 የኮሌጅ ትምህርት ተማሪዎች በመጀመሪያ ዓመት በኮሌጁ መሰረታዊ የንድፈ ሃሳብ ትምህርት ከተማሩ በኋላ ሁለተኛው ዓመት በመስክ የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት እና በሦስተኛው ዓመት ተመልሰው በኮሌጁ የሚማሩበት የትምህርት መርሐግብር ነው።

Open Education = የርቀት ትምህርት የዕድገት ደረጃ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ከመደበኛው ትምህርት ሥርዓት የወጣ ነው። ተማሪዎች የፈለጉትን በፈለጉበት ቦታ ሆነው ይማራሉ።

# ክፍል ሁለት
# ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑና ወደ አንድ አጠቃላይ ድምዳሜ ሊያደርሱ የሚያስችሉ በተለይም በርቀት ትምህርት ላይ ያጠነጠኑ ድርሳናትን ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

## 2.1 የርቀት ትምህርት ምንነት

የርቀት ትምህርት ምንነት በተለያዩ የመስኩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ሲገለጽ ቆጥቷል፤ ይሁን እንጂ ለዚህ ጥናት በሚያመች መልኩ የተወሰኑትን እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል፡፡

«የርቀት ትምህርት አብዛኛውን ጊዜ ቀደም ብለው በጽሁፍ በተዘጋጁ ወይም በተለያዩ መሣሪያዎች ላይ በተቀረጹ ይዘቶች አማካይነት በርቀት ከሚገኙ መምህራን ትምህርት የሚገኝበት ሂደት ነው፡፡ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል የጊዜና የቦታ ግንኙነት የተዘወተረ አይደለም» (Rowntree 1992:29)፡፡

ይኸው ሐሳብ በ Keegan እንደሚከተለው ተስፋፍቶ ተገልጾአል፤
በርቀት ትምህርት፣ አብዛኛው የትምህርቱ ሂደት የመምህር- ተማሪ የፊት ለፊት ግንኙነት የማይኖርበት ነው፣ የጽሑፍ፣ የድምጽ፣ የምስል፣ ወዘተ. ሚዲያዎች የአንድን ትምህርት ይዘት ወደ ተማሪው እንዲያደርሱ የሚደረግበት በተጨማሪም  አልፎ አልፎ ከሚደረገው የፊት ለፊት ወይም በተለያዩ መገናኛ ሚዲያዎች (መሳሪያዎች) አማካይነት ከሚደረግ ግንኙት በስተቀር የመምህሩና የተማሪዎች ግንኙነት የተዘወተረ አይደለም፡፡  (Keegan 1996:50)፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የSTRIDE ምሁራን የርቀት ትምህርትን ከተልዕኮ ትምህርትና ከ (open Education) ጋር በማነጻጸር እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

| የተልእኮ ትምህርት | የርቀት ትምህርት | **open Education** |
|---|---|---|
| -ሕትመት<br>-ፖስታ<br>-መደበኛው ሥርዓተ ትምህርት | ሕትመትን ጨምሮ ዘመኑ በፈቀደው ቴክኖሎጂ ይጠቀማል፡፡<br>ፖስታን ጨምሮ ዘመኑ በፈቀደው ቴክኖሎጂ ይጠቀማል፡፡<br>የተልዕኮ ትምሕርት የዕድገት ደረጃ ነው፡፡ | -የርቀት ትምህርት የዕድገት ደረጃ ነው፡፡<br>-ሙሉ በሙሉ ከመደበኛ ትምህርት ሥርአት ባሕርይ የወጣ ነው፡፡<br>-ተማሪዎች የፈለጉትን በፈለጉት ቦታ ሆነው ይማራሉ፡፡ |



ልዩነታቸው ሥርዓተ ትምህርትና ቴክኖሎጂ ነው፡፡

የሚያገናኛቸው የርቀት ትምህርት ልምድ መዳበር ወደ (Open education system) በቀላሉ መሸጋገር ያስችላል፡፡

ምንጭ (STRIDE 2000: ES-311:B2:13)

Perraton (1988; 34-45)፣ Keegan (1993:100) የገለጹት የርቀት ትምህርት ምንነት ለጥናቱ በሚይስፈልግ መልኩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የርቀት ትምህርት በትምህርት ሰጪው አካልና በተማሪዎች መካከል የቦታና የጊዜ ርቀት ወይም ክፍተት ኖሮ፡-ትምህርት ሰጪውንና ትምህርት ተቀባዩን አካል ቴክኖሎጂው

የሚያገናኝበት ሲሆን ይህም ማለት ጽሑፍ/ህትመት/ ሬዲዮ፣ ቴፕ፣ ቴሌቪዥን፣ ቪዲዮ፣ ኮምፒውተር፣ ኢንተርኔት፣ ወዘተ.፣አልፎ አልፎ የታቀደና ለአጭር ጊዜ የፊት ለፊት ግንኙት የሚኖርበት፣ በተለያዩ ምክንያቶች በመደበኛው መርሐግብር ማዳረስ የማይቻለውን ትምህርት ለማዳረስ የሚቻልበት፣ የአካል ጉዳት ኖሮባቸው በመደበኛው ሥርዓት ለማለፍ ለማይችሉ ምቹ የሆነ የመማሪያ ድባብ ለመፍጠር ያስችላል፣የሥራ ቦታቸውንና ቤተሰባቸውን ትተው ሙያቸውን ማሻሻል ለማይችሉ ዕድል የሚሰጥ ወዘተ. ትምህርት ማስፋፊያ ሥርዓት ነው፡፡

የሥራ አካባቢያቸውን መራቅ እንዲሁም ከቤተሰቦቻቸው መለየት የማይችሉ ነገር ግን ሙያቸውን በትምህርት ማሻሻል የሚፈልጉ፣ በተለያየ የእድሜ ክልል የሚገኙ፣ በተለያየ ቦታ የሚኖሩ፣ በተለያየ አካላዊ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎች እና የአካል ጉዳተኞች በርካታ ናቸው፡፡ ይህንን አስመልክቶ STRIDE (2001 ES-311-B.2:25) በመሬት ተፈጥሯዊ አቀማመጥ እና በቦታ ርቀት ምክንያት ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡ በገንዘብ አቅም ማነስ ምክንያት ለረዥም ጊዜ በመደበኛው የትምህርት ሥርዓት ማለፍ የማይችሉ፣ በክፍል ውስጥ ከብዙ ተማሪዎች ጋር በመቀመጥ ለመማር ሥነ-ልቦናዊና ማኅበራዊ ጫና አለብን ብለው ራሳቸውን የሚያስጨንቁ፣ የተለያዩ ማኅበራዊና አገራዊ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች የማኅበረሰቡ አካል ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ካልቻሉ ትምህርቱ ወደ እነሱ የሚሄድበትን መንገድ መንግሥታት ሊያመቻቹ እንደሚገባ ያስረዳል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ Rumble (1992:19-23) በመደበኛው መርሐግብር መማር የማይችሉትን እስከ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ተማሪዎችን ፍላጎት በርቀት ትምህርት ማሟላት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም Perraton (1993: 1-3) የርቀት ትምህርት በተለይ በማደግ ላይ ባሉ ሃገሮች የትምህርትን ሥርጭት ለማስፋፋት፣ የመምህራንን የሙያ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለማሻሻል እንዲሁም የትምህርትን ጥራት ለመጠበቅ ከፍተኛ እገዛ እያደረገ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ባጠቃላይ የርቀት ትምህርት በመደበኛው ትምህርት መርሐግብር የማይሸፈኑ የትምህርት ችግሮችን በመቅረፍ የመደበኛውን ትምህርት መርሐግብር ሊያግዝ የሚችል የትምህርት ሥርዓት ነው፡፡

## 2.2 የርቀት ትምህርት ተማሪ ባሕርይ

በ STRIDE ምሁራን (2000: ES-312, 18-19) በተገለጸው መሠረት በመደበኛው የትምህርት ሂደት የሚያልፉ ተማሪዎች የተወሰኑት ካልሆኑ በስተቀር አብዛኞቹ በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ያሉ፣ በተመሳሳይ የመማር ማስተማር ሂደት ያለፉና የተቀራረበ ልምድ ያላቸው ናቸው። እነዚሁ ምሁራን የርቀት ትምህርት ተማሪዎች በሌላ በኩል ከላይ ከቀረበው እጅግ የተለየ ባሕርይ እንዳላቸው ይገልጻሉ።እድሜያቸው በጣም የተራራቀ፣ ወጣቶችና በእድሜ የገፉ ሊሆኑ ይችላሉ።በተመሳሳይ መርሐግብር የሚሳተፉ በጥቅሉ ሲታይ የተመሳሰለ የስልጠና ደረጃ ያላቸው ሊሆኑ ቢችሉም፣ ዕውቀቱ የተገኘበት ጊዜና ስርአተ ትምህርት፣ ትምህርታቸውን ያቋረጡበት ሁኔታ እጅግ ሊለያይ ይችላል። ከሥልጠና በኋላና በአዲስ መርሐግብር መጀመሪያ መካከል ያሳለፉት የተለያየ ሕይወት ለመለያየታቸው አሉታዊም አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል።ሥልጠናው ከሚሰጥበት ተቋም በተለያየ ርቀትና በተለያየ አካባቢ የሚኖሩ ናቸው።በሥራና በተለያየ ምክንያት የጊዜ፣ የማጥኛ ሥፍራ፣ ወዘተ. ችግር ያለባቸው ሊሆኑ ይችላሉ።አብሯቸው የሚማር ባለመኖሩ ብቸኝነት የሚሰማቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ መጻሕፍት በአካባቢያቸው ባለማግኘታቸው በፈለጉበት ጊዜ የሚያማክሩት መምህር ባለመኖሩ፣ ወዘተ. በራስ የመተማመን ስሜት የሚያሳጣቸው፣ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

## 2.3 የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ባሕርይ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በርቀት ትምህርት መምህርና ተማሪ ከሚገናኙባቸው የመማር ማስተማር ሚዲያዎች ውስጥ ሕትመት (Print Medium) ይጠቀሳል። የቅርብ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፣ የሕትመት ሚዲያ (Print Medium) በርቀት ትምህርት ሂደት በከፍተኛ ሁኔታ በማገልገል ላይ ይገኛል።

ምንም እንኳን በአንባቢ አንበብቦ የመረዳት ችሎታ መሠረት የሚወሰን ቢሆንም አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሕትመት በቀላል ወጪ ሊዘጋጅ (Cost effective)ና በቀላሉ ሊስተካከልና ሊከለስ የሚችል ነው። ከሌሎች ሚዲያዎች ጋር በቀላሉ ሊቀናጅ የሚችልና ተማሪዎች በራሳቸው የመማር ስልትና ፍጥነት እንዲማሩ የሚያመች ነው፣ በተጨማሪም ብቻውን ለማስተማሪያነት ሊያገለግል የሚችል ነው፤ለዚህም ማስረጃ ሊሆን የሚችለው የርቀት ትምህርት ሲጀመር ብቸኛ የትምህርት ማስተላለፊያ ሆኖ መቆየቱ ነው። ( STRIDE 2001, ES-318,B2:11-13)

በሕትመት የሚቀርብ ትምህርት በምንም ዓይነት ቅርጽ ይቅረብ ተማሪዎች ሊጠቀሙበት የሚችሉት ወይም የተጠበቀው የባሕርይ ለውጥ መምጣት የሚችለው ትኩረት ተሰጥቶት ሲዘጋጅ ነው፡፡

ተማሪዎች ዕገዛ ከሚያደርጉላቸው መምህራን ጋር በግንባር ለረዥም ቆይታ የማይገናኙ፣ በአካባቢያቸውም የሚረዳቸው ግለሰብ ወይም የሚጠቀሙባቸው ማጣቀሻ የመረጃ ምንጮች በቀላሉ ማግኘት የማይችሉ እንደሚሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም የርቀት መማሪያ ሞጁዩሎች እንደ መምህር ሆነው እንዲያስተምሩአቸው፣ አስፈላጊውን ሁሉ መረጃ በተቻለ መጠን አጠናቅረውና አካተው ሊይዙ ይገባል፡፡ አቀራረባቸውም ቀላልና ግልጽ ሆኖ በጥንቃቄ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ሞጁዩሎች በተቻለ መጠን ተጨማሪ ማጣቀሻ መጻህፍት ሳያስፈልጋቸው በራሳቸው የሚያስተምሩ፣ የሚያነቃቁና፣ ለመማር የሚያነሳሱ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሞጁዩሎች ለንባብ በሚያመች መልኩ ተመጥነው ይቀርባሉ፡፡

ትምህርትን በርቀት ለማስፋፋት ሲታሰብ ዋናውና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ተማሪው ነው፡፡ ቀደም ባለው ክፍል እንደተጠቀሰው ከተማሪው ባሕርይ በመነሳት እንደጓደኛም፣ እንደመምህርም፣ ወዘተ. በመሆን የሚያነጋግረውና የሚፈለገውን ዕውቀት ክህሎትና አመለካከት የሚያመጣበት ሞጅዩል ሊኖረው ይገባል፡፡

Melton (2000:5) « የርቀት ትምህርት ሥርዓት ለተማሪው ቀጥተኛ ምላሽ የሚሰጥ፣ ተማሪውን ማዕከል ባደረገ መማር ላይ የሚያተኩር ነው» በማለት ያስረዳሉ፣ በተጨማሪም እኚሁ ምሁር (2002:21) «የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ለተማሪው መማሪያ ብቻ ሳይሆን ማማከሪያም ነው፡፡» በማለት ሃሳቡን ያጠናክራሉ፡፡ ይህም የሚከተለውን ሐሳብ የሚደግፍ ነው፡፡ ለርቀት ተማሪዎች ታስቦ የሚዘጋጅ ሞጁዩል የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡፡ ተማሪዎችን ምን እንደሚጠበቅባቸውና እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የሚናገር፣ የትኩረት ነጥቦችን በተለያየ መንገድ በየደረጃው የሚደጋግም፣ ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ተግባር ምን ያህል ጊዜ መስጠትና ለፕሮጀክት ሥራዎች እንዴት ማቀድ እንዳለባቸው የሚገልጽ፣ አሰልቺነት እንዳይኖር በመጠን በመጠኑ የተደራጀ፣ ቀደም ሲል ከተማሩት ጋር እየተዛመደ የሚያድግ፣ ማንበብ ብቻ ሣይሆን የተለያዩ ተግባራትን እየሠሩ በንቃት የሚሳተፉበት፣ በየደረጃው መጋቢ ምላሽ የሚያገኙበት እና ይዘቱን በአግባቡ እየተረዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት፣ እስከመጨረሻው ለመሄድ የሚያበታታቸው፣ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ (STRIDE 2000: ES-312-B2:21)፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

ባጠቃላይ ለርቀት ትምህርት ተማሪዎች በሚዘጋጅ ሞጁዩል፣ ተማሪው ኮርሱን በሚመለከት ከሚያገኘው ዕውቀት ክህሎችና አመለካከት በተጨማሪ የምክር አገልግሎት የሚያገኙበትም ነው።

## 2.4 የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት ሂደት

የርቀት ሞጁዩል (ኮርስ) አዘገጃጀት ሂደትን በሁለት ዋና ዋና ደረጃዎች ከፍለን ለማየት እንችላለን። የመጀመሪያው አጠቃላይ ሂደትንና ሁለተኛው የኮርሱን ዝግጅት የሚመለከት ነው፤

### 2.4.1 የኮርስ ዕቅድ

በርቀት ትምህርት የኮርስ ዝግጅት በቅድሚያ ከፍተኛ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ የኮርስ ዕቅድ ማውጣት እጅግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች በተዘጋጀ ሞጁዩል ላይ ለሚኖራቸው ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ አለ።

የኮርስ ዕቅድም በሚከተሉት ደረጃዎች ያልፋል፤

ሀ. የፍላጎት አሰሳ፣ የፍላጎት አሰሳ በተለያዩ ውሳኔዎች ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ሲሆን በተለያዩ የጥናት ዘዴዎች ይሰበሰባሉ።

ለ. ዓላማ መንደፍ፣ የሚፈለገውን ወይም የሚጠበቀውን በግልጽ ማስፈር ሲሆን፣ ዓላማ ለኮርስ አዘጋጆች ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ ሰነድ ነው።

ሐ. የግብአትና የዕጥረት ግምገማ፣ በዚህ ግምገማ ያለው ወይም የሚገኘው ባለሙያ የገንዘብ መጠን ፣ የሚያስፈልገው ሚዲያ፣ወዘተ. ይለያል።

መ. መስፈርቶችን ማውጣትና የአቀራረብ ዘዴዎች ማማረጥና ማቀናጀት።

ሠ. ሙከራ ማድረግ።

ረ. ግምገማ፣ በሁለት መንገድ ሊደረግ ይችላል፦ አንደኛው የተወሰኑ መጠይቆችን በማዘጋጀት ከተማሪዎች መረጃ በመሰብሰብ ሲሆን ፣ ሁለተኛው ከአስተባባሪዎች ፣ ከአሰልጣኞች፣ እንዲሁም ከቱቶሮች መረጃ በመሰብሰብ ይካሄዳል ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

### 2.4.2 የኮርስ ዝግጅት

የኮርስ ዝግጅት ሦስት ዋና ሂደቶች ያልፋል፤

ሀ. ርዕሶችን ወይም ይዘቶችን ማደራጀት፣ ይዘቶች ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ ከቀላል ወደ ከባድ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ ደረጃ በደረጃ እያደጉ በሚሄዱበት መንገድ ቅደም ተከተል ጠብቀው ይደራጃሉ።

ለ. የየምዕራፉን ቢጋር ማዘጋጀት።

ሐ. ይዘትን መጻፍ ወይም ማስፋፋት፣ እያንዳንዱ ርዕስ ወይም ይዘት ማስተዋወቅ፣ ማብራራት፣ ማጠናከር፣ በቅደም ተከተል ያሉበት ሲሆን እንደአጠቃላይ መርህ ሁሉም ርዕሶች ወይም ይዘቶች ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል። (STRIDE 2001 ES-312-B3:9-11) ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከርቀት ተማሪዎች ባሕርይ አንጻር የሚዘጋጁት መማሪያዎች ተማሪዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ሊረዱና ሥነ- ትምህርታዊ ጠቀሜታ (Pedagogical) ሊሰጡ በሚችሉበት መንገድ ሊደራጁ ይገባል። በመሆኑም አጠቃላይ የሞጁዩሉ ክፍል በሚከተሉት ዋና ዋና ክፍሎች ሊደራጅ ይችላል።

1. የመክፈቻ ክፍል (opening section):- ይህ ክፍል ተማሪዎች ሞጁዩሉን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት የሚረዳ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፤

- ብሩህ የሆነና ቀለሙ የሚስብ፣
- በተወሰኑ ቃላት የተጻፈ ርዕስ፣
- የምዕራፎች ዝርዝር፣
- ተማሪዎች ምን እንደሚጠቀምባቸው የሚያመላክቱ በግልጽ የተነደፉ ዓላማዎች፣ በርቀት ትምህርት መማሪያዎች ውስጥ የዓላማ በግልጽ መስፈር፤
    - ተማሪዎች ምን እንደሚጠቀምባቸው መረጃ ይሠጣሉ፣
    - ትምህርቱን ግልጽ ያደርጋሉ፣
    - ተግባሮችና ፕሮጀክቶች በቀላሉ እንዲሠሩ ያመቻቻሉ፣
    - ተማሪዎች ግንዛቤአቸውን እንዲከታተሉ ያስችላሉ፣
    - ትኩረት የሚሰጣቸውን (የሚገባቸውን) ነጥቦች ወይም ይዘቶች ይጠቁማሉ።



UNIVERSITY ... IES LIBRARY

❖ የሞጁዩሉን ወይም የምዕራፉን ይዘት የሚያስገነዝብ አነቃቂና ሳቢ በሆነ መንገድ የተጻፈ፣ ተገቢ መረጃ የሚሰጥ ተማሪውን ለንባብ የሚገፋፋና የሚመሩ ሐሳቦችን የያዘ መግቢያ፤

2. ዋና አካል (Main Text) ፡- ተገቢ ዋቢዎችን መሠረት በማድረግ በበቂ ሁኔታ የተዘጋጁ የመማሪያ ተግባራትን (Learning activities) የያዘ ዋና ክፍል ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ይይዛል፤

- ማስታወስና ሐሳቦችን ማዋሃድ ያስችል ዘንድ ባልተጨናነቀ ሁኔታ አጠር አጠር ብለው የተደራጁ በቀላል ቋንቋ የሚቀርቡ ናቸው፡፡
- የተማሪዎችን የመነሳሳት (Motivation) ቀጣይነት ሊያረጋግጡ የሚችሉ የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችን (Active learning) ያካተተ መሆን አለበት፡፡
- መረጃዎችን የበለጠ ለማዋሐድና ለማጠናከር /Concretize/ የሚያስችሉ ተገቢነት ያላቸው ልዩ ልዩ መግለጫዎችን ያካትታል፡፡
- ተማሪዎች ዓላማዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ፣ ግንዛቤአቸውን እና ዕድገታቸውን እንዲቆጣጠሩ፤ የራሳቸውን አስተያየት እንዲያንጸባርቁ፣ ልምዶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ፣ በአጠቃላይ በማማር ሂደቱ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ፣ በየጣልቃው በአጭር ርቀት የሚገቡ መልመጃዎች (In text exercises ) ተግባሮችንና የራስ መገምገሚያ ጥያቄዎችን ያካትታል፡፡

exercises text In text exercises

3. መዝጊያ (Ending) ፣ ዘርዘር ባለ መንገድ ቀርበው የነበሩ መረጃዎች በሰንጠረዥ፣ በስዕላዊ መግለጫ፣ በተወሰኑ ቃላት ወይም ዓ.ነገሮች፣ ወዘተ. አጠር ብለው የሚቀርቡበት የማጠቃለያ ክፍል ሲሆን የፕሮጀክት ስራዎችንና የቤት ሥራዎችን ያካትታል፡፡ ይህም ተማሪዎች ያነበቡትን እንዲያጠናክሩና በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው፡፡ (Lockwood 1998:16፣118፣**119**)፡፡

## 2.5 የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ግምገማ

ከርቀት ትምህርት ባሕርያት አንጻር፣ ለተማሪዎች የሚዘጋጁ የመማሪያ ሞጁዩሎች ትኩረት እንደሚገባቸው የዘርፉ ምሁራን በጥናቶቻቸው ጠቁመዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Melton (2002:5) እና Judith (1994:86)፣ የርቀት ትምህርት አንዱ ትኩረት የርቀት መማሪያ ማዘጋጀት ነው፤ በመሆኑም ለርቀት ትምህርት ተብለው የሚዘጋጁ ሞጁዩሎች በየጊዜው ሊፈተሹ፣ ሊስተካከሉና ሊከለሱ ይገባል፡፡



UNIVERSITY

STRIDE (2000:ES-312) እንደሚገልጹት የርቀት ትምህርት ማስተማሪያ አዘገጃጀት ሂደት ያዘገጃጀት ንድፍ ማውጣት፣ ማዘጋጀት፣ መገምገም፣ ማስተካከል እንዲሁም መከለስን በዋናነት ያካትታል። በርቀት ትምህርት መርሐግብር ከተማሪዎች፣ ከመምህራን፣ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች መጋቢ ምላሽ በመሰብሰብ ሞጅዮሉን ማስተካከልና መከለስ የማያቋርጥ ሂደት ነው። ይህም የኮርሱን ተገቢነት ጥራት፣ እንዲሁም ወቅታዊነት ፣ ለመጠበቅ ያስችላል።

Judith (1994:86) ግምገማ የተለያዩ አቀራረቦች ቢኖሩትም፣ የሚከተሉትን ደረጃዎች ሊያልፍ እንደሚችል ያስረዳሉ።

- አዘጋጆች ጓደኞቻቸው የታያቸውን አስተያየት ይጠይቃሉ፤
- አርታዕያን እንዲፈትሹት ይደረጋል፣
- በታላሚ ተማሪዎች ላይ ይሞከራል፣
- በአውደ ጥናት ይገመገማል፣
- መርሐግብሩ እንደተጀመረ ይገመገማል፣
- የሙሉ ዑደት ወይም የአንድ ጊዜ አጠቃላይ ውጤቱ ይጠናል።

የመፃሕፍት ግምገማ ውጪያዊና ውስጣዊ ግምገማ በመባል ይከፈላል። ውጭያዊ ግምገማ ሽፋን፣ መግቢያ እና የይዘት ዝርዝርን ይመለከታል፤ ውስጣዊ ግምገማ ደግሞ የይዘት አቀራረብ፣ ቅደም ተከተል፣ የተግባሮችና የይዘት ዝምድና፣ አነቃቂ ይዘቶች... ያካትታል (McDonough and Christopher 1994 63-79) ። በተጨማሪ Grant (1987:121 ) በመጽሐፍ ግምገማ ሂደት ማራኪነትን ፣ከተማሪዎች ደረጃ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ፣ ግልፅነትን ፣ አደረጃጀትን ፣ አላማን ከግብ የሚያደርስ መሆኑን፣ ወዘተ. መፈተሽ እንደሚገባ ያስረዳሉ።

### 2.5.1 የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ክለሳ

ምንም እንኳን በተለያዩ ደረጃዎች ጥንቃቄ ተደርጎበት የሚዘጋጅ ቢሆንም ቀደም ባለው ክፍል እንደተገለጸው፣ ሞጁዩልን ማስተካከል እና ወቅታዊ ማድረግ በርቀት ትምህርት ሂደት ዋናው ተግባር ነው። የሞጁዩል መከለስ ሥራ በአጭር ጊዜ የሚከናወን ባይሆንም የማስተካከል ሥራ ግን ሞጁዩሉ በስራ ላይ በዋለ የመጀመሪያ አመት ውስጥ ወዲያውኑ የሚከናወን ነው። (STRIDE ES-312-B3)።



UNIVERSITY LIBRARY

ለሞጁዩል ማስተካከል ሥራ መረጃ የሚሰበሰበው፣ተማሪዎች በየምእራፉ እንዲሞሉት በተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ ወይም የመቆጣጠሪያ ቅጽ ስለሆነ የጽሑፍ መጠይቆቹ በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤ ይህንን በሚመለከት Judith (1994:98) ሲገልጹ፣ በርቀት ትምህርት ሂደት በተዘጋጁ ሞጅዩሎች ላይ ለሚደረግ ጥናት የሚዘጋጁ መጠይቆች ለማንኛውም ሞጅዩል ዝግጅት የሚደረገው ጥንቃቄ ያስፈልጋቸዋል:: የሚፈለገውን ያህል መረጃ የሚያስገኙ፣ ሳያሰለቹ የሚሞሉ፤ በሥርዓት የተደራጁ፣ ግልጽ መመሪያ ያላቸው፣ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የግል ደብዳቤ ከአጥኝው ክፍል ቢኖራቸው ይመረጣል:: የግል ደብዳቤው የሚያትተው የጽሑፍ መጠይቁን የመሙላት ጠቀሜታ ሞጅዩሉን ከማሻሻል አኳያ መሆኑን ሲሆን በተጨማሪም መጠይቁን የሚሞሉት ተማሪዎች የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል:: በተጨማሪም ከተማሪዎች የቤት ሥራ ውጤት መረጃ ይሰበሰባል::

ተማሪዎች ስለኮርሱ አጠቃላይ ሁኔታ ሞልተው እንዲልኩ በሚዘጋጁ የአስተያየት ቅጾች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በሚከተለው መልኩ ሲደራጁና ሲዘጋጁ ይችላሉ::

| ገጽ | ርዕስ | መሥመር | የተፈጠረው ስሕተት | ተስተካክሎ ሲፃፍ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

ምንጭ፦(STRIDE 2000:ES-312 – B2-60)

ለሞጁዩል ክለሳ ሥራ መረጃ ፣ ከማሪዎች የአስተያየት ማህደር፣ለተማሪዎች እገዛ ከሚያደርጉ መምህራን ፣ከባለሙያዎች፣ ከአጥኚዎች ግምገማ፣ከአማካሪዎች አስተያየት፣ከቀደሞ ተማሪዎች ፣በመጀመሪያው ሂደት ከተደረጉ ጥናቶች፣ እንዲሁም ከተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት ወይም የባሕርይ መዝገብ እንደሚሰበሰብ STRIDE ( 2000: ES-312:62)ያስረዳል ::

## 2.5.2. የርቀት ትምህርት ሞጁዩል መገምገሚያ ከቅርጽና ከይዘት አደረጃጀት አንጻር

ቀደም ባለው ክፍል እንደተጠቀሰው የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ እና በታለመለት መሰረት ሞጁዩሉ እያገለገለ መሆኑን ለመፈተሽ መስፈርቶች ያስፈልጋሉ:: ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፤

❖ መዋቅርና ቅርጽ /Structure and layout /

- ሞጁዩሉ አይታን ይስባል ?
- የፊደሎች ቅርጽና መጠን ለርቀት ተማሪ ምቹ ነውን?
- መልስ ለመስጠት እና ማስታሻ ለመያዝ በቂ ቦታ አለውን?
- ከገጽ ወደ ገጽ፤ ከይዘት ወደ ይዘት፤ ከኋላ ወደ ፊት እንደስፈላጊነቱ ለመከታተል ምልክቶችና መመሪያዎች ግልጽ ናቸውን?

❖ ዓላማዎች

- ዕውቀት፤ ክህሎት እና አመለካከትን የሚለኩ ናቸውን?
- ተጨባጭ፤ ግልጽና በተማሪው ባሕርይ የተገለጹ ናቸውን?
- ከይዘት ጋር የሚዛመዱ እና አመላካች ናቸውን?

❖ መግቢያ

- በእያንዳንዱ ምእራፍ ወይም ክፍል በሚስብና በሚያስገነዝብ መንገድ በጥንቃቄ ተዘጋጅቷልን?

❖ ሥእሎች፤ ቻርቶች፤ ሰንጠረዦች፤ ግራፎች

- ገላጭ ናቸው /Self explanatory/

❖ ይዘት /Content material/

ከዓላማ ጋር የተዛመደ መሆኑን ፤

ከቀላል ወደ ከባድ በቅደም ተከተል የተደራጀ መሆኑን፤

- በግልጽ እና በቀላል አገላለጽ በማያሻማ መልኩ የቀረበ ነውን?
- ተገቢና በቂ ነውን?
- ያልተጨናነቀ እና ያልተንዛዛ ነውን ?
- የሂደት መከታተያ ጥያቄዎች ወይም ተግባሮች በተያያዘ መልኩ እና በአጭር ርቀት ይገኛሉን?
- የግምገማ ተግባሮች ተገቢ ምላሽ ወይም ማመሳከሪያ አላቸውን?

❖ ማጠቃለያ

- ግልጽና አስታዋሽ ነውን?
- በአጭሩ ለመከለስ ያግዛልን?

የሚሉትና የመሳሰሉት ጥቄቶቹ ተጠቃሾች ናቸው:: (STRIDE ES- 312: B3: 72,73)



ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

## 2.6 ለመደበኛው ትምህርት የሚዘጋጁ መጻሕፍትና ለርቀት ትምህርት የሚዘጋጁ መጻሕፍት ንጽጽር

በተግባር እንደሚታየው የርቀት ትምህርትን ከሌሎች የትምህርት መርሐግብሮች ከሚለዩት ውስጥ የተለያዩ ሚዲያዎችን በማቀናጀት መጠቀሙ፣ የይዘቶች አደረጃጀትና የመጋቢ ምላሽ (Feedback) ሂደቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: (STRIDE 2001:ES-311-B4:37)

በመስኩ የተገኙ ልምዶች እንደሚጠቀሙት፤ በተገቢ ሁኔታ የተደራጁ የርቀት ትምህርት መማሪያ ከሌሎች መጻሕፍት በእጅጉ የተለየ ነው:: ለርቀት ትምህርት ተብለው የሚዘጋጁ መጻሕፍት ዋናው ተግባራቸው Function ተማሪዎች እንዲማሩባቸው የሚያነሳሱ ተግባራትን ማጉላት ሲሆን በሌላ መልኩ የሚዘጋጁት መጽሕፍት ዋናው ተግባር የጸሐፊውን አተያይ ማጉላት ነው::

ለርቀት ተማሪዎች የሚዘጋጁ መጽሀፍት የመምህሩን አለመኖር ከግምት ውስጥ በማስገባት ተማሪዎችን እንዲያነቡ በሚያበረታታ መንገድ የተደራጁ መሆን አለባቸው:: ከዚህም በተጨማሪ የተጻፈውን መረጃ ማንበብ ብቻ ሳይሆን እየተመራመሩ እንዲማሩ የሚያደርግ አደረጃጀት ሊኖራቸው ይገባል :: ተገቢ አደረጃጀት የርቀት ትምህርትን ውጤታማ ያደርጋል::

በመደበኛና በርቀት ትምህርት መልክ በሚዘጋጁ መጽሐፍት መካከል ያለውን ልዩነት LockWood (1998) ሲገልጹ ምንም እንኳ ሁሉም መደበኛ መጽሐፍት (text book) አመቺ አይደሉም ወይም ሁሉም ከመደበኛው ትምህርት መርሐግብር ውጪ ለሚማሩ ተማሪዎች የሚዘጋጁ መጽሐፍት (Self-instructional materials) የተዋጣላቸው ናቸው ባይባልም የርቀት ትምህርት መማሪያዎች አዘገጃጀትን ተከትለን በሁለቱም መካከል ያለውን ልዩነት እንደሚከተለው የተወሰኑት ቀርበዋል፤



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

| ለመደበኛው ትምህርት የሚዘጋጁ መጽሐፍት | ለርቀት ትምህርት የሚዘጋጁ መጽሐፍት |
| --- | --- |
| • ዓላማዎች ውስንናቸው፤ስርጭታቸው እናሳ ነው::<br>• የመጽሀፉ ዝግጅት የመምህርን መኖር ታሳቢ የሚያደርግ ነው:: | • ምን ጊዜም ዓላማዎች በግልጽ ይዘረዘራሉ::<br>• ተማሪዎች በራሳቸው የሚማሩበትን ሂደት ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው:: |
| • ይዘቶች የተጨናነቁ ናቸው::<br>• የሂደት መከታተያና የራስ መገምገሚያ ላይኖራቸው ይችላል ቢኖሩም በተወሰነ ደረጃ ነው::<br>• ማጠቃለያ አልፎ አልፎ ሊኖረው ይችላል::<br>• ማስታወሻ ለማያዝ፤ የሂደት መከታተያ ተግባሮችን ለመስራት ታስቦ የሚዘጋጅ ቦታ የላቸውም ወይም ውስን ናቸው::<br>• የአጠናን ዘዴን ላያመለክቱ ይችላሉ::<br>• ተማሪዎች ለመጻፍ መሻሻል አስተያየት የሚሰጡበት ሁኔታ የተመቻቸ አይደለም:: | • ይዘቶች ምንጊዜም ከተወሰነላቸው የማንበቢያ ሰዓት አንፃር ተመጥነው የሚቀርቡ ናቸው::<br>• የሂደት መከታተያዎች የራስ መገምገሚያዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው በየይዘቱ ጣልቃ እየገቡ ይደራጃሉ::<br>• በየክፍሉ ማጠቃለያዎች በሰንጠረዝ፣ በስዕላዊ መግለጫ በተወሰኑ ዓ.ነገሮች፣ በጥያቄ መልክ ተቀናጅተው ወይም በአንዱ ዓይነት ይቀርባሉ::<br>• ማስታወሻ ለመያዝም ይሁን የተለያዩ ተግባሮችን ለመስራት ይቻል ዘንድ ክፍት ቦታዎች ሆን ተብለው ይዘጋጃሉ ወይም ይተዋሉ::<br>• ያስፈልጋሉ የተባሉ የአጠናን ዘዴዎች ይጠቆማሉ::<br>• ተማሪዎች መጽሐፉን እንዲገመግሙት ወይም አስተያየት በመስጠት ዝግጅቱ የተሻለ እንዲሆንና ወደፊት ለሚማሩት የተመቻቸ እንዲሆን እድል የሚሰጥ ነው:: |

ምንጭ፡ (Lockwood 1998:10-12)

በተጨማሪም Devloping Learning Modules በሚል ርዕስ ከድኅረገጽ የተገኘው መረጃ እንደ ሚያረጋግጠው በመደበኛው የትምህርት ሥርዓት በተለያየ መንገድ ማለፍ ወይም መሳተፍ ለማይችሉ የሚዘጋጅ ሞጁዩል የተለያየ ቅርጽ ሊኖረው ቢችልም የሚከተሉትን በዋናነት ሊያካትት ይገባል፤ ተተኳሪዎችን ከግምት ያስገባ፣ ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ ከቀላል ወደ ከባድ የተደራጀ ይዘት፣ ግልጽነትና ወጥነት ያላቸው መመሪያዎች፣ ግልጽነት ያላቸውና ተፈላጊ ይዘቶች ብቻ፣ በየጣልቃው መዘንጋትን ለመቀነስ የሚያገለግሉ የክለሳ ነጥቦች ወይም ስልቶች (Richardson:1-8)::



UNIVERSITY LIBRARY

## 2.7 በቋንቋ ትምህርት ዝግጅት የሚቀረጹ ዓላማዎችና ይዘቶች ዝምድና

የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች መነሻ የሚያደርጉት የተማሪውን ወይም የህብረተሰቡን ፍላጎት ነው። የሚቀረጹትም ሥነ ትምህርታዊ ጠቀሜታ ሊሰጡ በሚችሉበት መንገድ ወይም በተማሪው ባሕርይ ሊሆን ይገባል። በተገቢው መንገድ የተቀረጹ ዓላማዎች የሚከተሉት ባሕርያት ይኖሯቸዋል፤ ተገቢውን የትምህርት ይዘት ለመምረጥ ያስችላሉ፤ የሚፈለገውን የባህርይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ለመምረጥና ተግባራዊ ለማድረግ ጠቃሚ ይሆናሉ፤ እንዲሁም የግምገማ ስልቱን ለመወሰን ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው፤ ይህንን አስመልክቶ Grant (1987፣10) ሲገልጹ ቋንቋውን ታላሚው ተማሪ ለምን እንደሚማረው በግልጽ ማስቀመጥ ምን ዓይነት መጻሕፍት ተዘጋጅቶ በምን ዓይነት ዘዴ ትምህርቱ መቅረብ እንዳለበት ያሳያል።

የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች መገለጽ ያለባቸው ከመምህሩ አንፃር ሳይሆን ከተማሪው አንጻር መሆን እንዳለበት ምሁራን ያስረዳሉ። የይዘቶች አመራረጥ ቀደም ሲል በዓላማ አመራረጥ እንደተገለጸው መነሻ የሚያደርገው የተማሪውን ባህል፣ ልምድ፣ ፍላጎት፣ ወዘተ. ሆኖ የሚፈለገውን የባሕርይ ለውጥ ማምጣት መቻሉ ታይቶ ነው። ይህንን አስመልክቶ Mamidi (1984: 42) ስለሚመረጡ ይዘቶች የሚከተሉትን ነጥቦች አቅርበዋል፤

- ከተማሪው ልምድ፣ ፍላጎት፣ ገጠመኝና ባህል ጋር የሚጣጣሙ
- ዓላማውን በተገቢው መንገድ ከግብ የሚያደርሱ መሆን እንዳለባቸው ያስረዳሉ።

UNIVERSITY ... LIBRARY

# ክፍል ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

በዚህ ርዕሥ ሥር ጥናቱን ለማካሄድ የተመረጠው ዘዴና የመረጃ አሰባሰብ መሳሪያዎች በዝርዝር ይቀርባሉ።

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ (Descriptive) የምርምር ዘዴን መሠረት ያደረገና በተለይም ዓይነታዊ የትንተና ዘዴን በመጠቀም የሠነድ ፍተሻ ላይ ያተኮር ነው።ይህም የጥናት ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በጥናቱ ርዕሥ ላይ እንደተመለከተው ጥናቱ የመጽሐፍ ግምገማ መሆኑና ለዚህም ይህ የጥናት ዘዴ ተስማሚ ሆኖ መገኘቱ ነው።ለዚህም ዘዴ እንደመረጃ ምንጭ የሚያገለግሉት መዝገቦች፣የተለያዩ የትምህርት ነክ ጽሑፎች፣መርሃትምህርቶች ወዘተ.እንደሆኑ በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን ያስምሩበታል። (Best እና Khan 1999:191) ።የሠነድ ፍተሻን ዓላማ አስመልክቶም ከሚቀርቡ ማስረጃዎች መካከል በጽሐፍትና በሌሎች የህትመት ውጤቶች ውስጥ ያለውን የይዘት አቀራረብ የክብደትና የቅለት ደረጃ ለመለየት፣በሠልጣኞች ሥራዎች ውስጥ የሚታዩ ግድፈቶችን ለመተንተን የሚጠቀሱ ናቸው።(Best እና Khan 1999:192) ።

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ. በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ በ1998 ዓ.ም ለርቀት ትምህርት መርሐግብር የተዘጋጀ ኮሌጅ አማርኛ (Amha 101) የርቀት ትምህርት ሞጁዩል፤

ለ. በኮሌጁ ትምህርታቸውን በርቀት ተከታትለው አሁን በሥራ ላይ ካሉ እና በ2000 ዓ.ም ትምህርታቸውን በርቀት እየተከታተሉ ከሚገኙ ተማሪዎች ውስጥ በናሙና የተመረጡ የሞጁዩሉ ተጠቃሚዎች፤

ሐ. በኮሌጁ ኮርሱን በርቀት የሚያስተምሩ እና በተዘረጋላቸው የቱቶሪያ መርሐግብር መሰረት ለተማሪዎቹ እገዛ የሚሰጡ መምህራን ፤

መ. ሞጁዩሉን ያዘጋጁ መምህራንና፣

ሠ. የኮሌጁ የርቀት ትምህርት መርሐግብር አስተባባሪዎች ናቸው።

የርቀት ተማሪዎች የሞጁዩሉ ቀጥተኛ ተጠቃሚ በመሆናቸው፤ እንዲሁም በሞጁዩሉ ዝግጅት የተሳተፉና ኮርሱን በማስተማርና ለተማሪዎቹ እገዛ በመስጠት ላይ ያሉት መምህራን ስለ ሞጁዩሉ ጥንካሬና ድክመት ከተማሪዎቹ ቀጥተኛ መጋቢ ምላሽ /Feedback/ የሚያገኙ በመሆናቸው በመረጃ ምንጭነት ተፈላጊ ሆነዋል፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

### 3.3.1 ኮሌጅ አማርኛ /Amha 101/ የርቀት ሞጅዩል ናሙና

ይህ ሞጁዩል የተመረጠበት ምክንያት ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ የዋለ በመሆኑና በይዘትና ቅርጽ አደረጃጀቱ ላይ በአንጻራዊ መልኩ ከሌሎች ሞጁዩሎች ይበልጥ ሰፊ መጋቢ ምላሽ ይገኛ በሚል እሳቤ ነው፡፡

### 3.3.2. የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ

የጊዜን፣ የገንዘብንና የአቅምን ተጽዕኖዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀደም ሲል ኮርሱን በርቀት ተከታትለው በአሁኑ ሰአት በማስተማር ላይ ካሉት መምህራን ውስጥ በምቾት ናሙና በአቅራቢያ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት በቁጥር 40 የሚሆኑ መምህራን ተመርጠው 22 ሴቶችና 10 ወንዶች የተዘጋጀላቸውን የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተው መልሰዋል፡፡በአሁኑ የትምህርት ዘመን ትምህርቱን በርቀት እየተከታተሉ ካሉት ተማሪዎች ውስጥ የቱቶሪያል አጋጣሚን በመጠቀም በቁጥር 100 የሚሆኑት የፆታን ተባልጦ ከግምት ውስጥ በማስገባት በይሁንታ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ተመርጠው 37 ሴቶችና 49 ወንዶች የተዘጋጀላቸውን የጽሁፍ መጠይቅ ሞልተው መልሰዋል፡፡

### 3.3.3. የሞጁዩል አዘጋጆች እና የርቀት መርሐግብር አስተባባሪዎች ናሙና አወሳሰድ

የሞጁዩሉ አዘጋጆች ከነበሩት የተገኙት በቁጥር 7 ስለሆኑ ሁሉም የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጎ ሁሉም ሞልተው መልሰዋል፤እንዲሁም አንድ የርቀት አስተባባሪ ለጥናቱ ዓላማ መሳካት አስተዋጽኦ ስለሚኖራቸው በጥናቱ ተካተዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት በሥራ ላይ የዋሉት የሰነድ ትንተና፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ-መጠይቅ ናቸው።

### 3.4.1 የሰነድ ትንተና

ጥናቱ የሚያተኩረው በኮሌጅ አማርኛ /Amha 101/ የቅርጽና የይዘት አደረጃጀት ፍተሻ ላይ በመሆኑ ቀደም ሲል በጥናቱ ክልልና ገደብ ርዕሥ ሥር የተዘረዘሩትን የትኩረት ነጥቦች በክፍል ሁለት በክለሳ ድርሳን ስለርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጃት በስፋት የተጠቀሱትን መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ የመቆጣጠሪያ ዝርዝር / Amha 101/ ሞጁዩሉን ለመፈተሽ በሥራ ላይ ውሏል፡ እነዚህንም በአባሪ ሦስት ይመለከቷል።

### 3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ቀደም ባለው ክፍል በክለሳ ድርሳን ሥር ስለርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት የተጠቀሱትን መነሻ ያደረገ ነው ። ዝግ እና ክፍት የሆኑ የጽሑፍ ጥያቄዎች ከተማሪዎችና ከአዘጋጆች ጠቃሚ መረጃ ለመሰብሰብ ተዘጋጅተው ተሰራጭተዋል፤ለቀድሞ ተማሪዎች ከተሰራጨት 40 የጽሑፍ መጠይቆች ውስጥ 32(80%) እንዲሁም በ2000 ዓ.ም. ኮርሱን በመውሰድ ላይ ላሉ ተማሪዎች ከተሰራጨት 100(86%) ተሞልተው ተመልሰዋል። ቃለመጠይቆችም እንዲሁ ከርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት ሂደት አንጻር ተቀርጸው በጥናቱ ለተካተተው የርቀት ትምህርት አስተባባሪ ቀርበው መረጃ ተሰብስቧል።

## 3.5 የአተናተን ዘዴ

በመጀመሪያ ጥናቱ ያተኮረባቸው የሞጁሉ ክፍሎች ክለሳ ድርሳኑን መሠረት በማድረግ በተዘገጁ የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት መስፈርቶች መሠረት በዓይነታዊ የትንተና ዘዴ ተፈትሸዋል፤ ቀጥሎ ተማሪዎችና መምህራን የሞሏቸው የጽሑፍ መጠይቆች ውጤቶች በሰንጠረዥ ተደራጅተው በአሀዛዊ የትንተና ዘዴ በመቶኛ ተገልጸዋል። በተጨማሪም በቃላት ተተንትነዋል። በቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃም ተተርጉሟል። ከዚያም የሦስቱንም መረጃዎች ተዛምዶ መሠረት በማድረግ ማጠቃለያ በመስጠት በተገኘው ውጤት መሰረት የመፍትሄ ሃሳብ ለመጠቆምም ተሞክሯል።



HAWASSA UNIVERSITY IKB LIBRARY

# ክፍል አራት

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል በሰነድ ትንተና፣ በጽሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ፣ ኮርሱን በርቀት መርሐግብር ከተከታተሉና እየተከታተሉ ካሉ ተማሪዎች፣ ሞጁዩሉን ካዘጋጁት መምህራንና ለተማሪዎቹ ቱቶሪያል ወይም እገዛ ከሚሰጡ መምህራን እንዲሁም ከኮሌጁ የርቀት ትምህርት ክፍል የተሰበሰቡ መረጃዎች በክፍል ሁለት፣ በክለሳ ድርሳን ከቀረበው ጽንሰሐሳብ ጋር እየተዛመዱ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 4.1 የሰነድ ትንተና ውጤት

### 4.1.1 የሞጅዩሉ ቅርጽ

ስለ ቅርጽ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች፡- ዕይታን መሳብ፣ የፊደሎች መጠን፣ የማስታወሻ መያዣና የመልስ መስጫ ቦታዎች፣ መመሪያዎች እና ልዩ ልዩ ምልክቶች ናቸው።

ሞጁዩሉ በA4 ወረቀት በኮምፒውተር ተጽፎ ከተባዛ በኋላ የተጠረዘ ነው። የውጪ ሽፋን ገጽ የኮርሱን ስም፣መለያ ቁጥር፣ መርሐግብሩንና የተዘጋጀበትን ኮሌጅ በጽሑፍ ከመግለጹ ሌላ ከመርሐግብሩ ጋር ተያያዥነት ያለው ሥዕላዊም ሆነ ሌላ መግለጫ የለውም፤ ብሩህ አይደለም፣ ውስጣዊ ገጽታውም ቢሆን የተጨናነቀና ግልጽ የሆነ ቦታ ጉልቶ የማይታይበት ነው። በመሆኑም ዕይታን ስቦ ለንባብ ይገፋፋል የሚያስብል አይደለም።

በሞጁዩሉ ውስጥ የተለያየ መጠን ያላቸው ፊደሎች ይገኛሉ። በውጪ ሽፋን ገጽ ላይ የሚገኙ መረጃዎች በኮምፒውተር ጽሕፈት በ10፣14፣18፣24 መጠን (Font) የተጻፉ ሲሆን ከመግቢያው ጀምሮ እስከ ማጠቃለያው ያለው ይዘት በአብዛኛው በ10 መጠን (Font) የተጻፈ ነው። ይህም በእያንዳንዱ ገጽ ላይ መጨናነቅን በመፍጠሩ በተለይ የማየት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች እንደፈለጉት እንዳያነቡ እንቅፋት ሊሆንባቸው ይችላል። በሁለተኛው ዙር የተሰራጨው ሞጁዩል የፊደሎች መጠን (Font) ከ 10 ወደ 12 አድጎ የተዘጋጀ ነው ።

Font Font Font

እያነበቡ ማስታወሻ ለመያዝ የሚያስችል ሆን ተብሎ የተተወ ቦታ የለም። እንዲሁም ለመልስ መስጫነት የተዘጋጁ ቦታዎችም በአብዛኛው በቂ አይደሉም፤ ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ሰፊ ማብራሪያ የሚፈልጉና ምሳሌዎች እንዲሰጡባቸው የሚጠይቁ ናቸው።

በሞጁዩሉ ውስጥ መግቢያ፣ የመልመጃ ጥያቄዎች፣ የራስ መገምገሚያ ጥያቄዎች፣ የማገናዘቢያ ጥያቄዎች እንዲሁም የተግባራትና የራስ መገምገሚያ መልሶችን /ማመሳከሪያዎችን/ የሚያመለክቱ ስድስት ምልክቶች ሲኖሩ፣ በሞጁዩሉ የመጀመሪያው ክፍል ከነትርጉማቸው ቀርበዋል። ውስን፣ ግልጽና አብዛኞቹ በወጥነት በመስፈራቸው እንደአስፈላጊነቱ ከገጽ ወደ ገጽ፣ ከፊት ወደኋላ በማገናዘብ ለማንበብ የሚያግዙ ናቸው።/ ምልክቶቹንና ትርጉማቸውን በአባሪ አንድ ይመለከቷል/።

ይሁን እንጂ በገጽ 17፣ በክፍል አንድ፡ "የቃላት ምንነትና አመሠራረት" የሚለውን ርዕስ መሠረት በማድረግ የተሰጠው ተግባር ሁለት ምልክት የለውም፤ በተጨማሪም በሞጁዩሉ የመጀመሪያ ክፍል "የምልክቶች መፍቻ" በሚል ርዕስ ሥር "የተግባራትና የራስ መገምገሚያ መልሶች" ተብሎ የተገለጸው ምልክት በዝርዝር ይዘቱ ውስጥ የሚጠቁመው "የራስ መገምገሚያ" እንጂ "ተግባራትን" አይደለም፤ ይህም ይዘቶቹ የተለያየ ምልክት እንደሚያስፈልጋቸው ጠቋሚ ነው።

#### 4.1.2 የሞጁዩሉ የይዘት አደረጃጀት

ሞጁዩሉ በአጠቃላይ አምስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። እያንዳንዱ የሞጁዩሉ ዋና ዋና ክፍል (ምዕራፍ) ይዘትም ከቀላል ወደ ከባድ የተደራጀ ነው። አምስቱም ክፍሎች መክፈቻ /Opening section/ ፣ ዋና አካል /Main text/ እና መዝጊያ /Ending section/ እንዲኖራቸው የተደራጁ ሲሆን ዝርዝር ይዘታቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል።

##### 4.1.2.1 መክፈቻ /**Opening section/**

በዚህ ክፍል የተካተቱ ዋና ዋና ይዘቶችን የሚያስገነዝቡ፣ አነቃቂና ሳቢ በሆነ መንገድ የተጻፉ፣ መረጃ በመስጠት ተማሪውን ለንባብ የሚገፋፉና የሚመሩ ሐሳቦችን የያዙ ዓረፍተ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ነገሮች እና ከተማሪዎች የሚጠበቁትን የባህሪ ለውጦች የሚያመላክቱ ዓላማዎች ሰፍረዋል። የዚህ ጥናት ዋና ተተኳሪ የሆኑትም ዓላማዎች እንደሚከተለው ይተነተናሉ፤

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በሞጁዩሉ ውስጥ አምስት ዋና ዋና ክፍሎች ሲኖሩ በእያንዳንዱ ክፍል በአማካይ አምስት በድምሩ ሃያ አምስት ዓላማዎች ተዘርዝረዋል። የተዘረዘሩን ዓላማዎች ለመፈተሽ በመስፈርትነት የተወሰዱት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፤

- የዓላማዎች ከይዘት ጋር መዛመድ፣
- የዓላማዎች ከተግባሮች እና ከመልመጃዎች ጋር መዛመድ፣
- የዓላማዎች ግልጽ መሆን፣
- የዓላማዎች አመላካች መሆን፣
- የዓላማዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት የሚያነሳሱ መሆን፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በዚህም መሠረት በሞጁዩሉ የቀረቡት ዝርዝር ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው። ከሠንጠረዥ አንድ እስከ ሠንጠረዥ አምስት የሚያመለክቱት የዓላማዎችንና የይዘቶችን ዝምድና ነው።

ሠንጠረዥ አንድ፡- የክፍል አንድ ዓላማዎች ዋና ዋና ይዘቶች

| ክፍል | ዓላማዎች | ዋና ዋና ይዘቶች |
|---|---|---|
| አንድ | የዚህን ክፍል ካጠናቀቃችሁ በኋላ፣<br>1. የቃላትን ምንነት ታብራራላችሁ።<br>2. በንግግር ድምጽና በዘረድምፅ መካከል ያለውን ልዩነት ትዘረዝራላችሁ።<br>3. በምእላድና በቃል መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ታስረዳላችሁ።<br>4. ለአዲስ ቃል ምሥረታ መንስኤው ምን እንደሆነ ትገልጻላችሁ።<br>5. የቃላት አመሠራረት ሥርዓቶችን ታብራራላችሁ። | የቃላት ምንነትና አመሠራረት<br>- የቃላት ምንነት<br>- ምዕላድ<br>- ቃልና ምዕላድ<br>የቃላት አመሠራረት<br>- አዲስ ቃል መፍጠር<br>- ቅጥያዎችን በመጨመር ቃላት የመመሥረት ሂደት<br>- በማሳጠር ቃል የመመሥረት ሂደት<br>- ውሰት |



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ከሠንጠረዥ አንድ የምንረዳው በተራቁጥር 1፣ 3፣ 4 እና 5 የተዘረዘሩት ዓላማዎች የሚፈለገውን የባሕርይ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ልምዶች በሞጁዩሉ ውስጥ እንዳሏቸው በግልጽ ይታያል ። በተራ ቁጥር 2 የተነደፈው ዓላማ ከይዘቶች ጋር የሚዛመድበትን ሁኔታ ከሰንጠዘገፍ አናይም። ይሁን እንጂ በሞጁዩሉ ውስጥ በገጽ 4 በመልመጃ መልክ ቀርቦ በተከታታይ ገጾች በስፋት ማብራሪያ ተሰጥቶበታል። በተራ ቁጥር 1 ከተነደፈው ዓላማ ጋር የሚዛመደው ይዘት የቃላት ምንነት ነው። በተራ ቁጥር 3 ከተነደፈው ዓላማ ጋር የሚዛመደው ይዘት ምዕላድ እንዲሁም ቃልና ምዕላድ የሚለው ይዘት ነው። በተራቁጥር 4 እና 5 ከተነደፉት ዓላማዎች ጋር የሚዛመዱት ይዘቶች አዲስ ቃል መፍጠር፣ ቅጥያዎችን በመጨመር ቃላት የመመሥረት ሂደት፣ በማሳጠር የመመሥረት ሂደትና ውሰት የሚሉ ይዘቶች ናቸው።

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የክፍል ሁለት ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች

| ክፍል | ዓላማዎች | ዋና ዋና ይዘቶች |
|---|---|---|
| ሁለት | ይህንን ትምህርት አጥንታችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፣<br>1. በቀጽሞውና በአሁኑ የሰዋስው ሊቃውንት መካከል ያለውን የቃላት አከፋፈል ልዩነት ትዘረዝራላችሁ።<br><br>2. ዘመናዊ የአማርኛ የሰዋስው ሊቃውንት ቃላትን ለመከፋፈል የሚጠቀሙባቸውን መስፈርቶች ማስረጃ እየሰጣችሁ ታብራራላችሁ።<br><br>3. እያንዳንዱ የቃል ክፍል ከሌላው የቃል ክፍል በምን እደሚለዩ ምሳሌ እየሰጣችሁ ታስረዳላችሁ።<br><br>4. የቀረበላችሁን የቃላት ዝርዝር ከሰዋስው አንፃር በየወገናቸው ትመድባላችሁ። | የቃላት ዓይነቶች<br>- ቃላት ከሰዋሰው አንፃር አዴት ይከፈሉ ነበር?<br>- ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው ሊቃውንት የአማርኛ ቃላት አከፋፈል መስፈርት ያደረጉት ምንድን ነው?<br>- በዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው ሊቃውንት የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ዓይነቶች<br>  - ስም<br>  - ግሥ<br>  - ቅጽል<br>  - ተውሳከ ግሥ<br>  - መስታዋድድ<br>- ቃላት ከሰዋስው አንጻር እንዴት ይከፈላሉ? |

በሠንጠረዥ ሁለት መሠረት በክፍል ሁለት ከተራ ቁጥር 1-4 የተዘረዘሩት ዓላማዎች ተማሪዎች እንዲለማመዱባቸው ከተመረጡ ይዘቶች ጋር በአብዛኛው መዛመዳቸው ይታያል።በተራ ቁጥር 1፣2 እና 3 ከተነደፉት ዓላማዎች ጋር የሚዛመዱት ይዘቶች ቃላት

ከሰዋስው አንጻር እንዴት ይከፈሉ ነበር?፣ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው ሊቃውንት የአማርኛ ቃላት አከፋፈል መስፈርት ያደረጉት ምንድነው?እና በዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው ሊቃውንት የአማርኛ ቃላት ዓይነቶች የሚሉት ናቸው፡፡ በተራ ቁጥር 4 ከተነደፈው ዓላማ ጋር የሚዛመደው ይዘት ቃላት ከሰዋስው አንጻር እንዴት ይከፈላሉ? የሚለው ነው፡፡

ሠንጠረዥ ሦስት፡- የክፍል ሦስት ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች

| ክፍል | ዓላማዎች | ዋና ዋና ይዘቶች |
|---|---|---|
| ሦስት | በክፍሉ ይዘቶች በአግባቡ ከተለማመዳችሁ በኋላ፣<br>1. የቃላት አጠቃቀምን ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡<br>2. የቃላት አጠቃቀም ደረጃዎችን በምሳሌ አስደግፋችሁ ታስረዳላችሁ፡፡<br>3. የመደበኛና የኢመደበኛ ቃላት አጠቃቀምን ልዩነት ታብራራላችሁ፡፡<br>4. በመደበኛ ቃላት ተጠቅማችሁ ሐሳባችሁን በጽሑፍ ታቀርባላችሁ፡፡<br>5. በቃላት ምርጫ ወቅት ትኩረት የሚሹ መሠረታዊ ጉዳዮችን በዝርዝር ታብራራላችሁ፡፡ | **የቃላት አጠቃቀም ደረጃና የቃላት ምርጫ**<br>- የቃላት አጠቃቀም ምንድን ነው?<br>- አጠቃቀም ደረጃዎች<br>- መደበኛ የቃላት አጠቃቀም<br>- ኢመደበኛ የቃላት አጠቃቀም<br>- ዘዬ ቃላት<br>- ያራዳ ቃላት<br>- የሙያ ቃላት<br>- የባእድ ቃላት<br>- ጸያፍ ቃላት<br><br>**የቃላት ምርጫ**<br>- በአውዳዊ አገባብ<br>- በተመሳሳይ ፍቺ<br>- በአማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ<br>- በፈሊጣዊ ፍቺ<br>- ከወቅታዊነት አኳያ |

በሠንጠረዥ ሦስት መሠረት ከተራ ቁጥር 1-5 የተዘረዘሩት ዓላማዎች ተማሪዎቹ ከሚለማመዱባቸው ይዘቶች ጋር በአብዛኛው እንደሚዛመዱ ይታያል፡፡ ከተራ ቁጥር 1-4 ከተዘረዘሩ ዓላማዎች ጋር የሚዛመዱት ይዘቶች የቃላት አጠቃቀም ደረጃ እና የቃላት ምርጫ በሚል ዋና ይዘት ሥር የሚጠቃለሉት ናቸው፡፡ በተራ ቁጥር 5 ከተነደፈው ዓላማ ጋር የሚዛመዱት ይዘቶች የቃላት ምርጫ በሚለው ዋና ይዘት ሥር የሚጠቃለሉ ይዘቶቸ ናቸው፡፡



UNIVERSITY ... ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ አራት፡- የክፍል አራት ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች

| ክፍል | ዓላማዎች | ዋና ዋና ይዘቶች |
|---|---|---|
| አራት | ይህንን ክፍል ካጠናቀቃችሁ በኋላ፣<br>1. የዘይቤን ምንነትና ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ።<br>2. የዘይቤ ዓይነቶችን በመዘርዘር አንድነትና ልዩነታቸውን ታብራራላችሁ።<br>3. በሚቀርብላችሁ ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ዘይቤዎች በመለየት ጠቀሜታቸውን ታብራራላችሁ።<br>4. በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ዘይቤን በጠቀም ሐሳባችሁን ትገልጻላችሁ። | ዘይቤዎች<br>- የዘይቤ ምንነት<br>- የዘይቤ አይነቶች<br>- አነፃፃሪ ዘይቤ<br>- ተለዋጭ ዘይቤ<br>- ሰውኛ ዘይቤ<br>- እንቶኔ ዘይቤ<br>- ተምሳሌት ዘይቤ<br>- ምጸት ዘይቤ<br>- አያዎ ዘይቤ |

በሠንጠረዥ አራት መሠረት በክፍል አራት የተዘረዘሩትን የባሕርይ ለውጦች ለማምጣት ያስችላሉ የተባሉ የልምምድ ይዘቶች መኖራቸውን በአመዛኙ ማየት ይቻላል፤ይሁን እንጂ በተራ ቁጥር 1 የተነደፈውን ዓላማ ስንመለከት በሠንጠረገዡ ውስጥ ጠቀሜታን በሚመለከት የሚደረግ ልምምድ መኖሩን የሚጠቁም ይዘት አይታይም። በሞጁዩሉ ውስጥ ከገጽ 101 ጀምሮ የዘይቤን ምንነት ለማጉላት በቀረቡ ማብራሪያዎች ውስጥ በስፋት ጠቀሜታውን የሚያሳዩ ይዘቶች ቀርበዋል። ከተዘረዘሩት ዓላማዎች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶች ዘይቤዎች በሚል ዋና ርዕሥ ሥር ያሉ ይዘቶች ናቸው።

ሠንጠረዥ አምስት፡- የክፍል አምስት ዓላማዎችና ዋና ዋና ይዘቶች

| ክፍል | ዓላማዎች | ዋና ዋና ይዘቶች |
|---|---|---|
| አምስት | ከዚህ ክፍል በኋላ፣<br>1. የዓረፈተ ነገረን ምንነት ትገነዘባላችሁ።<br>2. መሠረታዊ የዓረፍተ ነገርን ክፍሎች ትለያላችሁ።<br>3. የዓረፍተ ነገር ማስፋፊያ ስልቶችን ተጠቅማችሁ ዓረፍተ ነገርን ታስፋፋላችሁ።<br>4. የተለያዩ የዓረፍተ ነገር ዓይነቶችን ትረዳላችሁ። | ዓረፍተነገር<br>- የዓረፍተ ነገር ምንነት<br>- የዓረፍተ ነገር መሠረታዊ ክፍሎች<br>- የዓረፍተ ነገር ዓይነቶች<br>- ዓረፍተ ነገርን ማስፋፋት |

በሠንጠረዥ አምስት መሠረት በክፍል አምስት ከተራ ቁጥር 1-4 የተዘረዘሩት ዓላማዎች ተማሪዎች የባሕርይ ለውጦቹን ለማምጣት የሚለማመዱባቸው ይዘቶቹ ምን እንደሆኑ ያሳያል።

ከላይ ከቀረቡት ከአምስቱም ሠንጠረዦች እንደምንረዳው፣

- ይዘቶቹ በአብዛኛው ከዓላማዎቹ የመነጩ ይመስላሉ፤ ይህም ዓላማዎቹ ከይዘት ጋር ያላቸው ተዛምዶ የጠበቀ መሆኑን ያሳያል።
- ዓላማዎቹ አመላካች መሆናቸው ተማሪዎች ለሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት ጠቋሚ በመሆን ያገለግላሉ፤ በመሆኑም ተማሪዎቹ ዓላማዎቹን በማንበብ የሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅትና የሚያነቡት ይዘት በአብዛኛው የሚጣጣም ነው።
- የተነደፉት ዓላማዎች አመላካችነት ለይዘት ብቻ ሳይሆን ምን ዓይነት ተግባራትና መልመጃዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ጠቋሚም ናቸው። ስለሆነም ተማሪዎች ምን እንደሚጠበቅባቸው በቅድሚያ ሊያውቁ ይችላሉ።

እነዚህ ዓላማዎች ከተግባሮች እና መልምጃዎች ጋር ያላቸውን ዝምድና በሚከተሉት ሠንጠረዦች እንመለከታለን፤

ሠንጠረዥ ስድስት፡- የክፍል አንድ ዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች

| የተዘረዘሩ ዓላማዎች | ተግባሮችና መልመጃዎች |
|---|---|
| አንድ- 1 | ቃላት ከምንና እንዴት እደሚመሠረቱ አብራሩ። |
| አንድ- 2<br>አንድ- 3 | - በንግግር ድምጽና በዘረድምጽ መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ።<br>- በቃላትና በምላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለጹ።<br>- የምላድን ምንነት በምሳሌ አስደግፋችሁ ግለጹ። |
| አንድ- 4 ፣ 5 | -ለአዲስ ቃል መፈጠር ምክንያቱ ወይም ሰበቡ ምንድን ነው?<br>- አዳዲስ ቃላት የሚመሠረቱበትን ሥርዓት / መንገድ/ አብራሩ። |

ማስታወሻ፡- አንድ፣ የሚያመለክተው ክፍሉን ወይም ምዕራፉን ነው።

1፣2፣3፣4፣5፣ የሚያመለክቱት ቀደም ሲል በሠንጠረዥ አንድ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ነው።

በሠንጠረዥ ስድስት መሠረት ያለውን የዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች ዝምድና ስንመለከት የቃላትን ምንት ታብራራላችሁ ለሚለው ዓላማ ቃላት ከምንና እንዴት እንደሚመሠረቱ አብራሩ፣ በንግግር ድምጽና በዘረድምጽ መካከል ያለውን ልዩነት ትዘረዝራላችሁ ለሚለው ዓላማ በንግግር ድምጽና በዘረድምጽ መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ፣ በምዕላድና በቃል መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ታስረዳላችሁ ለሚለው ዓላማ በምዕላድና በቃል መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለጹ የሚሉት ይገኙበታል።

ሠንጠረዥ ሰባት፡- የክፍል ሁለት ዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልምጃዎች

| የተዘረዘሩ ዓላማዎች | ተግባሮችና መልመጃዎች |
|---|---|
| ሁለት- 1 | በጥንታዊ ሰዋሰው የአማርኛ ቃላት በስንት ይከፈሉ ነበር? ክፍፍሉስ ምንን መሠረት ያደረገ ነበር? |
| ሁለት- 2 | -የዘመናችን የስነ ልሳን ሊቃውንት የቃላት አከፋፈል ምን መሠረት ያደረጋል? ለምን?<br>- በአምስት ብቻ የከፈሉበትስ ምክንያት ምንድን ነው? |
| ሁለት- 3፣4 | -ከስም ክፍል ከሚመደቡ የአማራኛ ቃላት ውስጥ 10 ያህል ዘርዝሩና ከስም ክፍል ለመመደባቸው ምክንያችሁን በዝርዝር አቅርቡ።<br>- ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ በስም ወገን የሚመደቡትን ለይታችሁ ፃፉ /አበረች፣ ሰማ፣ አስቀመጠ፣ ጠመኔ፣ቶሎ፣ ከበሮ፣ ቀረ፣ ጠረጴዛ፣ ተማረ፣ ፍየል፣ ፍላጐት/ |

ማስታወሻ፡- ሁለት ፤የሚያመለክተው ክፍሉን ወይም ምዕራፉን ነው።

1፣2፣3፣4 ፤የሚያመለክቱት ቀደም ሲል በሠንጠረዥ ሁለት የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ነው።

ሰማ
ጠመኔ

በሠንጠረዥ ሰባት መሠረት ያለውን የዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች ዝምድና ስንመለከት በቀድሞውና በአሁኑ የሰዋስው ሊቃውንት መካከል ያለውን የቃላት አከፋፈል ልዩነት ትዘረዝራላችሁ ለሚለው ዓላማ የዘመናችን የሥነ ልሣን ሊቃውንት የቃላት አከፋፈል ምንን መሠረት ያደረገ ነው፤ በአምስት ብቻስ የተከፈሉበትምክንያት ምንድን ነው፤የሚሉት ይገኙበታል ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

ሠንጠረዥ ስምንት፡- የክፍል ሦስት ዓላማዎች፣ ተግባሮች እና መልመጃዎች

| የተዘረዘሩ ዓላማዎች | ተግባሮች እና መልመጃዎች |
|---|---|
| ሦስት- 1፣2 | - አብዛኛውን ጊዜ በንግግርም ይሁን በጽሑፍ ላይ የማይውሉ ቃላት የምንላቸውን ምሳሌ በመስጠት አሳዩ።<br>- በአካባቢያችሁ ሰዎች በእለት ተእለት ተግባራቸው ውስጥ የሚያሳዩትን የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት ዘርዝሩ።<br>- በክፍል አንድ ስለቃል ምንነት ግንዛቤ ወስዳችኋል። ከዚህ በመነሳትስለቃላት አጠቃቀም ምንነት ማብራሪያ ስጡ።<br>- |
| ሦስት- 3 | - የኢ-መደበኛ ቃላትን ባሕርያት ዘርዝሩ። |
| ሦስት- 5 | - በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ሐሳብን በመግለጽ ሂደት የቃላት ምርጫ አስፈላጊ የሚሆንበትን ምክንያት በምሳሌ አስደግፋችሁ አስረዱ። |

ማስታወሻ፡- ሦስት = የሚያመለክተው ክፍሉን ወይም ምዕራፉን ነው።

1፣2፣3፣5= የሚያመለክቱት ቀደም ሲል በሠንጠረዥ ሦስት የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ነው።

በሠንጠረዥ ስምንት መሠረት ያለውን የዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች ዝምድና ስንመለከት የቃላት ያጠቃቀምን ልዩነት ትገልጻላችሁ ለሚለው ዓላማ በአካባቢያችሁ ሰዎች በዕለት ከዕለት ተግባራቸው ውስጥ የሚያሳዩትን የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት ዘርዝሩ፣ በቃላት ምርጫ ወቅት ትኩረት የሚሹ መሠረታዊ ጉዳዮችን በዝርዝር ታብራራላችሁ ለሚለው ዓላማ በንግግርም ይሁን በጽሑፍ ሃሳብን በመግለጽ ሂደት የቃላት ምርጫ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት በምሳሌ አስደግፋችሁ አስረዱ የሚሉት ይገኙበታል።

ሠንጠረዥ ዘጠኝ፦ የክፍል አራት ዓላማዎች፣ ተግባሮች እና መልመጃዎች

| የተዘረዘሩ ዓላማዎች | ተግባሮች እና መልመጃቻች |
|---|---|
| አራት- 2 | - ሰውኛ ዘይቤ ማለት ምን ማለት ነው? ማብራሪያ ስጡ።<br>- የተለዋጭ ዘይቤን እና የአነጻጻሪ ዘይቤን አንድነትና ልዩነት አብራሩ። |
| አራት- 3 | -በተሰጠው ግጥም ውስጥ የሰውን ባሕርይ የወረሰው ምንድን ነው?<br>- ከላይ የቀረበው ግጥም በምን ዓይነት ዘይቤ የቀረበ ነው? |

ማስታወሻ፦ አራት ፤የሚያመለክተው ክፍሉን ወይም ምዕራፉን ነው።

2፤3 ፤የሚያመለክቱት ቀደም ሲል በሠንጠረዥ አራት የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ነው።

በሠንጠረዥ ዘጠኝ መሠረት ያለውን የዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች ዝምድና ስንመለከት የዘይቤ ዓይነቶችን በመዘርዘር አንድነትና ልዩነታቸውን ታብራራላችሁ ለሚለው ዓላማ ሰውኛ ዘይቤ ማለት ምን ማለት ነው? የተለዋጭ ዘይቤንና የአነጻጻሪ ዘይቤን አንድነትና ልዩነት አብራሩ ፤ በሚቀርብላችሁ ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ዘይቤዎች በመለየት ጠቀሜታቸውን ታብራራላችሁ ለሚለው ዓላማ በተሰጠው ገጥም ውስጥ የሰውን ባሕርይ የወረሰው ምንድነው የሚሉት ይገኙበታል።

ሠንጠረዥ አሥር፦ የክፍል አምስት ዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች

| የተዘረዘሩ ዓላማዎች | ተግባሮች እና መልመጃዎች |
|---|---|
| አምስት- 3 | - ዓረፍተ ነገር ማስፋፋት ሲባል ምን ትገነዘባላችሁ?<br>- በሁለቱ የዓረፍተ ነገር ማስፋፊያ መንገዶች በእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት በድምሩ አራት ዓረፍተ ነገሮች ጻፉ። |

ማስታወሻ፦ አምስት ፤የሚያመለክተው ክፍሉን ወይም ምዕራፍን ነው።

3 ፤የሚያመለክተው ቀደም ሲል በሠንጠረዥ አምስት የተገለፀውን ዓላማ ነው።

በሠንጠረዥ አሥር መሠረት ያለውን የዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች ዝምድና ስንመለከት የአረፍተነገር ማስፋፍያ ስልቶችን ተጠቅማችሁ አረፍተነገር ታስፋፋላችሁ ለሚለው ዓላማ በሁለቱ የአረፍተነገር ማስፋፊያ መንገዶች በአያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት በድምሩ አራት አረፍተነገሮች ጻፉ የሚሉት ይገኙበታል።

ማስገንዘቢያ፦ በሠንጠረዥ ስድስት እስከ ሠንጠረዥ አሥር የተጠቆሙ ዓላማዎች፣ ተግባሮችና መልመጃዎች ከሞጁሉ ውስጥ ለናሙና የተወሰዱ ናቸው።

- ዓላማዎቹ ከጠቋሚነታቸው ባሻገር ከቀላል ወደ ከባድ መደራጀታቸውና በየይዘቱ ተመጥነው መገኘታቸው፣ ይዘቶችም ተመጥነው የተዘጋጁ መሆኑን ስለሚያመላክቱ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት የሚያነሳሱ ናቸው።
- አብዛኛዎቹ ዓላማዎች ግልጽና ሊለካ በሚችል መልኩ የተጻፉ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ጥቂት ዓላማዎች በጥቅል መልክ በመጻፋቸው በትክክል የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ የሚያመለክቱ ሆነው አልታዩም።

አስረጂ 1. በገጽ 121 «የዓረፍተ ነገር ዓይነቶችን ትረዳላችሁ» የሚለው አገላለጽ ተማሪዎቹ በምን ደረጃ መገንዘብ እንዳለባቸው ወይም ከተገነዘቡ በኋላ ምን እንደሚጠበቅባቸው ስለማያሳይ ግልጽ አይደለም።

አስረጂ 2. «የተለያዩ አረፍተ ነገር አይነቶችን ትረዳላችሁ» ይህኛውም አገላለጽ በአስረጅ 1 ከቀረበው የተለየ አይደለም። የመረዳት ደረጃውን እና ከመረዳት በኋላ የሚጠበቀውን የባሕርይ ለውጥ የሚጠቁም አይደለም።

### 4.1.2.2. ዋና አካል

ይህ ክፍል የተለያዩ ዋቢዎችን መሠረት በማድረግ በምዕራፍ ተከፋፍለው የተዘጋጁ የተለያዩ የመማሪያ ተግባራትን የያዘ ዋና ክፍል ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዩች የያዘ ነው፤

- በተለያዩ ርዕሶች የተደራጁ ይዘቶች፣
- «መልመጃ» በሚል ርዕስ የቀረቡ የተለያዩ ጥያቄዎች፣
- «ተግባር» በሚል ርዕስ የቀረቡ የተለያዩ መለማመጃዎች፣
- «ማገናዘቢያ» በሚል ርዕስ የቀረቡ የመቆጣጠሪያ ዝርዝሮች፣ እና



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

- «የራስ መገምገሚያ ጥያቄ» በሚል ርዕስ የቀረቡ የተለያዩ መለማመጃዎች፡

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እነዚህን የሞጁሉ ዋና አካል ይዘቶች ለመፈተሽ በመስፈርትነት የተወሰዱት ነጥቦች፣

- የቋንቋ አጠቃቀም ግልጽነት፣
- የይዘቶቹ በበቂ ሁኔታ መብራራት፣
- ለየይዘቱ የቀረቡ መግለጫዎች ወይም ምሳሌዎች በቂ መሆን፣
- የይዘቶቹ አደረጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ አቀራረብ መሆን፣
- የይዘቶቹ ያልተንዛዙ መሆን፣
- የይዘቶች በየምዕራፉ ተመጣጣኝ መሆን፣
- የተግባሮችና መልመጃዎች፣
    - አንቃቂ መሆን፣
    - ከዓላማ ጋር የተዛመዱ መሆን፣
    - የማመሳከሪያ መልሶች ተገቢ መሆን፣
    - የግል ጥረትን የሚያበረታቱ መሆን፣
    - በአጭር ርቀት የተደራጁ መሆን፣
    - በበቂ ሁኔታ የቀረቡ መሆን፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

«የቃላት አጠቃቀም ደረጃና የቃላት ምርጫ» በሚል ርዕስ ለቀረቡ ይዘቶች በምሳሌነት ከቀረቡት የቋንቋ አጠቃቀሞች ውጪ በሞጁሉ የቀረቡ ይዘቶች በአብዛኛው መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀምን የተከተሉ ናቸው። አብዛኞቹ አንቀጾች በአጫጭር ዓረፍተ ነገሮች የተዋቀሩ ናቸው። ይሁን እንጂ መጠነኛ የሆነ የፊደል ግድፈቶች እና ያጠቃቀም ስህተቶች ይስተዋላሉ፤

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሞጁዩሉ አምስት ምዕራፎች ሲኖሩት፣ የእያንዳንዱ ምዕራፍ ይዘት፡-

መክፈቻ፣

ዋና አካል፣ እና

መዝጊያ

በመባል ተከፋፍሎ የተደራጀ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
K.B LIBRARY

እነዚህ ክፍሎች ያላቸው ይዘት የርቀት ተማሪን ባሕርይ አገናዝቦ የተዘጋጀ በመሆኑ በበቂ ሁኔታ የተብራራ ነው። ይህም ማለት ተጨማሪ አጋዥ መጻሕፍትን ላያገኙ ወይም የቅርብ እገዛ የሚሰጣቸው ላይኖር እንደሚችል የታሰበበት ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ተግባሮች ከሞጁዩሉ ምላሽ ስለሌላቸው ለተማሪዎቹ አስቸጋሪ ናቸው።

አስፈላጊ በሆኑበት ቦታዎች መግለጫዎች እና ምሳሌዎች ከመቅረባቸውም በተጨማሪ የይዘቶቹ አደረጃጀት ከቀላል ይዘት ወደ ከባድ ይዘት የቀረበ ነው። ሁሉም ይዘቶች ያልተንዛዙና በየምዕራፉ የተመጣጠኑ በመሆናቸው በተማሪዎች ላይ መሰላቸትን የማይፈጥሩ ናቸው፤ ከዚህም በተጨማሪ በየአጭር ርቀት ላይ ተግባሮችና መልመጃዎች በበቂ ሁኔታ ከነማመሳከሪያዎቻቸው ስለተደራጁ ተማሪዎቹ ለንባብ ይገፋፋሉ።

ይሁን እንጂ ልዩ ልዩ ሚዲያዎች እንደ አመችነታቸው ተመርጠው ከሞጁዩሉ ጋር በትንጅት ቢቀርቡ ትምህርቱ የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆን ይታመናል። በክለሳ ድርሳኑ እንደተጠቀመው የርቀት ትምህርት አንዱ ባሕርይ የተለያዩ ሚዲያዎችን በቅንጅት የሚጠቀም መሆኑ ነው።

ቀደም ሲል «ዋና አካል» በሚል ርዕስ እንደተገለጸው የተግባሮችንና መልመጃዎችን ሁኔታ ለመፈተሽ በመስፈርትነት የተወሰዱት ነጥቦች፣ ከዓላማ ጋር የተዛመዱ መሆን፣ የተሰጡት ማመሳከሪያ መልሶች ተገቢ መሆን፣ በአጭር ርቀት የተደራጁ መሆን፣ በበቂ ሁኔታ የቀረቡ መሆን እና አነቃቂ መሆን የሚሉት ናቸው።
በዚህም መሠረት የተዘጋጁት ተግባሮችና መልመጃዎች የሚከተሉት ባሕርያት አሏቸው፤

የሚጠበቅ ምላሽ ወይም ማመሳከሪያ ከሞጁዩሉ መጨረሻ ላይ ያላቸው በሥራቸው በርካታ ጥያቄዎችን የያዙ ሃያ ስድስት አጠቃላይ ተግባሮች፣ እንዲሁም የመልስ መስጫ ቦታ የተተወላቸው እና ምላሾቻቸው ከምላ ጎደል ከቀጣዩ ማብራሪያ ጋር የሚዛመዱ በሥራቸው በርካታ ጥያቄዎችን የያዙ ሃምሳ ስድስት መልመጃዎች አሉ። ተግባሮችና መልመጃዎች ቀደም ሲል ከሠንጠረዥ ስድስት እስከ ሠንጠረዥ አሥር እንደተመለከተው የተነደፉ ዓላማዎችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው።



ADDIS ABABA UNIVERSITY I.E.S. LIBRARY

የማመሳከሪያ መልሶች እንደመነሻ የሚያገለግሉና ተማሪዎቹ ሙከራቸውን እንዲፈትሹበት የሚያገለግሉ ናቸው። ተማሪዎቹም ከራሳቸው ምላሽ ጋር በማነጻጸር ሁኔታዎችን ሰፋ አድርገው እንዲመለከቱ የሚጋብዙ ናቸው። ተግባሮቹና መልመጃዎቹ በየአጭር ርቀት የተደራጁ ከመሆናቸው በተጨማሪ በብዛት ወይም በበቂ ሁኔታ የቀረቡ በመሆናቸው ተማሪዎች ሞጅዩሉን በማንበብ ሂደት ወይም በሞጅዩሉ በመማር ሂደት በንቃት እንዲሳተፉ ያደርጋሉ።

ተማሪዎቹ በመተባበር እንዲሠሩ የሚጠይቁ መልመጃዎችና ተግባሮች መኖራቸው ተስፋ ሳይቆርጡ በመበረታታት እንዲማሩ ያግዛሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ተግባሮች የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ያላገናዘቡ ናቸው። ተማሪዎቹ በተለያየ ዘመን ትምህርታቸውን ያጠናቀቁና በተለያየ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ያለፉ መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል።

የአንዳንድ መልመጃዎች ምላሽ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ወዲያው ሞጅዩሉ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ምናልባት የግል ጥረትን ሳያበረታታ ይችላል።

#### 4.1.2.3 መዝጊያ (Ending section)

ይህ ክፍል ተማሪዎቹ የዘነጉት ይዘት ካለ እንዲያስታውሱና ወደኋላ ተመልሰው እንዲከልሱ የሚያደርግ ሲሆን በአምስቱም ክፍሎች አጠር ባለና ግልጽ በሆነ ሁኔታ የቀረበ ነው።

## 4.2. ከርቀት ተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተናና ትርጉም

### 4.2.1. የሞጅዩሉ ቅርጽ

የሞጁዩሉን ቅርጽ አስመልክቶ በመስፈርትነት የተወሰዱት ነጥቦች፤ የሞጁዩሉ ውጫዊ ገጽታ ለመማር የሚኖረውን የማነሳሳት ሁኔታ፣ የመመሪያዎችና ምልክቶች አመላካች መሆን፣ የፊደሉች መጠን ለእይታ አመች መሆን፣ ማስታወሻ ለመያዝ የተተው ቦታዎች እንዲሁም ለመልስ መስጫ የተተው ቦታዎች በቂ መሆን የሚሉት ናቸው።

እነዚህን መስፈርቶች፤ መሠረት በማድረግ የተማሪዎቹን ምላሽ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ተደራጅቶ እናየዋለን።

ሠንጠረዥ አሥራ አንድ፦ በ2000 ዓ.ም በመማር ላይ ካሉና ከቀድሞ ተማሪዎች የሞጅዩሉን ቅርጽ በሚመለከት የተሰበሰበ መረጃ

| መሥፈርት | በ2000 ዓ.ም. በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች | | | | የቀድሞ ተማሪዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አዎ | | አይደለም | | አዎ | | አይደለም | |
| | ቁ* | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| የሞጅዩሉ ውጫዊ ገጽታ ለመማር ያነሳሳል? | 41 | 47.67 | 45 | 52.33 | 8 | 25 | 24 | 75 |
| መመሪያዎችና እና ምልክቶች አመላካች ናቸው? | 74 | 86.05 | 12 | 13.95 | 28 | 87.5 | 4 | 12.5 |
| የፊደሎች መጠን ለዕይታ አመቺ ነውን? | 84 | 97.67 | 2 | 2.33 | 4 | 12.5 | 28 | 87.5 |
| ማስታወሻ ለመያዝ የተተው ቦታዎች በቂ ናቸውን? | 23 | 26.74 | 63 | 73.26 | 3 | 9.38 | 29 | 90.62 |
| ለመልስ መስጫ የተተው ቦታዎች በቂ ናቸውን? | 79 | 91.86 | 7 | 8.14 | 15 | 46.88 | 17 | 53.12 |

ቁ*= ቁጥር

ከሠንጠረዥ አሥራ አንድ የምንረዳው የሞጅዩሉ ውጫዊ ገጽታ ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን ተማሪዎች የመማር ፍላጎት የማያነሳሳ መሆኑን ነው፤ ከመቶ እጅ ሰባ አምስት የሚሆኑት የቀድሞ ተማሪዎች እና በ2000 ዓ.ም በመማር ላይ የሚገኙ ኀምሳ ሁለት ነጥብ ሰላሳ ሦስት ከመቶ የሚሆኑት የሚጠቁሙትም የሞጁዩሉ ውጫዊ ገጽታ ሳቢ አለመሆኑን ነው።

ከመቶ እጅ በአማካይ ከሰማንያ ሰድስት በላይ የሚሆኑት የሁለቱም ጊዜያት ተማሪዎች በሞጁዩሉ ውስጥ የሠፈሩት መመሪያዎችና ምልክቶች አመላካች መሆናቸውን ጠቁመዋል። ይሁን እንጂ የቁጥሩ ከፍተኛ መሆን ጉዳዩ ትኩረት እንዳይሰጠው የሚያደርግ አይደለም። በክለሳ ድርሳኑ መሠረት የርቀት ተማሪዎች ካላቸው ባሕርይ አንፃር መመሪያዎችና ምልክቶች ግልጽ መሆን ይኖርባቸዋል።

የፊደሎች ለዕይታ አመቺ አለመሆኑን ከሰማኒያ ሰባት ከመቶ በላይ የሚሆኑት የቀድሞ ተማሪዎች ሲጠቁሙ፣ የ2000 ዓ.ም ተማሪዎች ምላሽ ግን የተገላቢጦሽ ነው። ከመቶ እጅ ከዘጠና ሰባት በላይ የሚሆኑት የፊደሎች መጠን ለዕይታ አመች መሆኑን ጠቁመዋል። ይህም ልዩነት የተፈጠረው፣ ሞጁዩሉ በቀጣዩ ዙር የፊደሎች መጠን እንዲሻሻል ተደርጐ በመሠራጨቱ ነው።

ማስታወሻ ለመያዝ ሆን ተብሎ የተተው በቂ ቦታዎች በሞጁዩሉ ውስጥ አለመኖራቸውን የሁለቱም ጊዜያት ተማሪዎች ከሰጡት መረጃ መረዳት ይቻላል፤ ይሁን እንጂ ለመልስ መስጫ የተተው ቦታዎች አማካይ ምላሹ የሚጠቁመው በቂ መሆኑን ነው።

4.2.2 የሞጁዩሉ የይዘት አደረጃጀት

የሞጁዩሉን የይዘት አደረጃጀት አስመልክቶ ተማሪዎች ምላሽ ከሰጡባቸው ጉዳዮች ውስጥ በየይዘቱ የተነደፉ አላማዎች ከተተኳሪ ነጥቦች ውስጥ ይገኙበታል። በዚህም መሠረት የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ተደራጅቷል።

ሠንጠረዥ አሥራ ሁለት፡- በየምዕራፉ የተነደፉ ዓላማዎችን በሚመለከት የተሰበሰበ መረጃ

| መሥፈርት | በ2000 ዓ.ም. በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች | | | | የቀድሞ ተማሪዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አዎ | | አይደለም | | አዎ | | አይደለም | |
| | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት ያነሳሳሉ። | 69 | 80.23 | 17 | 19.77 | 27 | 84.38 | 5 | 15.62 |
| ከተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ያመለክታሉ ወይም ይጠቁማሉ። | 74 | 86.05 | 12 | 13.95 | 29 | 90.63 | 3 | 9.37 |
| ከተግባሮች እና መልመጃዎች ጋር ይዛመዳሉ። | 74 | 86.05 | 12 | 13.95 | 30 | 93.75 | 2 | 6.25 |

በሠንጠረዥ አስራ ሁለት መሠረት በየይዘቱ ስለ ተነደፉ ዓላማዎች በቀድሞዎቹም ይሁን በ2000 ዓ.ም. በመማር ላይ በሚገኙት ተማሪዎች ከሰማንያ ከመቶ በላይ በአዎንታ የተጠቆመ ነው። ይህም በየይዘቱ የተነደፉ ዓላማዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የሚያነሳሱ፣ ከተማሪዎች የሚጠበቀውን የባሕርይ ለውጥ የሚጠቁሙ ወይም የሚጠበቅባቸውን የሚያመላክቱ እንዲሁም ከተግባሮችና መልመጃዎች ጋር የሚዛመዱ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
I.E.S LIBRARY

ምንም እንኳን በሞጁዩሉ ውስጥ የተነደፉ ዓላማዎች ያላቸው ፋይዳ የጎላ ቢሆን ከመቶ እጅ በአማካይ ከአሥራ ሰባት በላይ የሆኑት የሁለቱ ጊዜት ተማሪዎች ዓላማዎቹ የመማር ፍላጎትን እንደማያነሳሱ አመልክተዋል። ከመቶ እጅ በአማካይ አሥራ ሁለት በላይ የሚሆኑት ዓላማዎቹ አመላካች አይደሉም፣ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን አይጠቁሙም ይላሉ። በተጨማሪም ከመቶ እጅ ከአሥር በላይ የሚሆኑት የሁለቱም ጊዜያት ተማሪዎች ዓላማዎቹ ከተግባሮችና መልመጃዎች ጋር የመዛመድ ሁኔታቸው አናሳ መሆኑን ይጠቁማሉ። ይህም ጉዳይ ከትምህርቱ ጥራት አንጻር ሲታይ ሞጁዩሉ መሻሻልና ተደጋግሞ መከለስ እንዳለበት የሚጠቁም ነው።

በሞጁዩሉ ውስጥ ያሉትን አጠቃላይ ይዘቶች በሚመለከት ተማሪዎቹ በተሰጣቸው መስፈርት መሠረት የሰጡትን ምላሽ እንደሚከተለው እናያለን፤

ሠንጠረዥ አሥራ ሦስት፡- በየምዕራፉ ስለ ይዘቶች የተሰበሰበ መረጃ

| መሥፈርት | በ2000 ዓ.ም. በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች | | | | የቀድሞ ተማሪዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አዎ | | አይደለም | | አዎ | | አይደለም | |
| | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| መጨናነቅ ይታይባቸዋል። | 77 | 89.53 | 9 | 10.47 | 30 | 93.75 | 2 | 6.25 |
| ግልጽነት ይጎድላቸዋል። | 72 | 83.72 | 14 | 16.28 | 30 | 93.75 | 2 | 6.25 |
| በበቂ ሁኔታ አልተብራሩም። | 69 | 80.23 | 17 | 19.77 | 28 | 87.5 | 4 | 12.5 |

በሠንጠረዥ አሥራ ሦስት መሠረት በአንዳንድ ርዕሶች ላይ የይዘት መጨናነቅ ይታያል የሚሉ የሁለቱም ጊዜያት ተማሪዎች በአማካይ ከመቶ እጅ ከዘጠና አንድ በላይ ሲሆኑ የተተሩት ሁሉም ይዘቶች መጨናነቅ ይታይባቸዋል ብለዋል።

ከመቶ እጅ በአማካይ ከሰማንያ ስምንት በላይ የሚሆኑት የሁለቱም ወቅት ተማሪዎች ግልጽነት የሚጎድላቸው አንዳንድ ይዘቶች እንዳሉ ሲጠቁሙ የተቀሩት ሁሉም ይዘቶች ግልጽነት እንደሚጎድላቸው ጠቁመዋል።

ከመቶ እጅ በአማካይ ከሰባ ስምንት በላይ የሚሆኑ የሁለቱም ወቅት ተማሪዎች በበቂ ሁኔታ ያልተብራሩ አንዳንድ ይዘቶች መኖራቸውን ሲጠቁሙ የተቀሩት ሁሉም ይዘቶች በበቂ ሁኔታ እንዳልተብራሩና ጉድለት እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

ተማሪዎቹ፡ - የቃላት ምስረታ

- ምዕላድ

- ዘይቤዎች

- አንዳንድ ማመሳከሪያ ምላሾች ተጨማሪ አጋዥ መጻሕፍት እንደሚያስፈልጋቸውና ቢቻል ትምህርቱ በሌሎች አጋዥ ሚዲያዎችም ቢደገፍ የሚመረጥ መሆኑን ጭምር ጠቁመዋል፡፡ በክለሳ ድርሳኑም እንደተገለጸው የምንረዳው የርቀት ተማሪዎች በልዩ ልዩ ሚዲያዎች መደገፍ እንዳለባቸው ነው፡፡

በመሆኑም መረጃው በየትኛውም መንገድ ይገለጽ፣ በሞጁዩሉ ውስጥ መጨናነቅ የሚታይባቸው፣ ግልጽነት የጐደላቸው እንዲሁም በበቂ ሁኔታ ያልተብራሩ ይዘቶች እንዳሉ የሚያመለክት ነው፡

ተግባሮችንና መልመጃዎችን በሚመለከት ተማሪዎች በተሰጣቸው መስፈርት መሠረት የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ተደራጅቶ ቀርቧል፤

ሠንጠረዥ አሥራ አራት፡ - ተግባሮችንና መልመጃዎችን በሚመለከት የተሰበሰበ መረጃ

| መሥፈርት | በ2000 ዓ.ም. በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች | | | | የቀድሞ ተማሪዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አዎ | | አይደለም | | አዎ | | አይደለም | |
| | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| አነቃቂ ናቸው፡፡ | 68 | 79.07 | 18 | 20.93 | 22 | 68.75 | 10 | 31.25 |
| ከዓላማ ጋራ ይዛመዳሉ፡፡ | 76 | 88.37 | 10 | 11.63 | 30 | 93.75 | 2 | 6.25 |
| ተገቢ ማመሳከሪያ አላቸው፡፡ | 60 | 69.77 | 26 | 30.23 | 24 | 75 | 8 | 25 |
| ፈጠራን ያበረታታሉ፡፡ | 66 | 76.74 | 20 | 23.26 | 22 | 68.75 | 10 | 31.25 |
| በበቂ ሁኔታ ቀርበዋል፡፡ | 60 | 69.77 | 26 | 30.23 | 25 | 78.13 | 7 | 21.87 |
| የግል ጥረትን ያበረታታሉ፡፡ | 78 | 90.70 | 8 | 9.30 | 28 | 87.5 | 4 | 12.5 |
| በመተባበር ለመማር ያስችላሉ፡፡ | 69 | 80.23 | 17 | 19.77 | 23 | 71.88 | 9 | 28.12 |

በሠንጠረዥ አሥራ አራት መሠረት የሁለቱም ወቅት ተማሪዎች ለተዘረዘሩት ሰባቱም መሥፈርቶች የሰጡት ምላሽ በአማካይ ከመቶው እጅ ከሰባ በላይ የሚሆነው አዎንታዊ ነው። በተለይ ተግባሮችና መልመጃዎችን ከዓላማ ጋር መዛመድ በአማካይ ከመቶ እጅ ከዘጠና በላይ መሆኑ ዓላማዎቹ ተማሪዎች ለሚሠሯቸው ተግባሮችና መልመጃዎች በከፍተኛ ሁኔታ ያዘጋጇቸው መሆኑን ያመለክታል።

ይሁን እንጂ አሉታዊ ምላሾቹ ከትምህርት ጥራት አንጻር ለወደፊት በሞጁዮሉ ክለሳ (Revision) ላይ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች መጠቆማቸው አልቀረም። የሁለቱንም ጊዜያት ተማሪዎች አማካይ ውጤት በመውሰድ አሉታዊ ምላሹን በዝርዝር ስንመለከት፣ ተግባሮችናመልመጃዎች አነቃቂ አይደሉም የሚሉት ከመቶእጅ ከሃያ አምስት በላይ ይሆናሉ። ተግባሮችና መልመጃዎች ከተነደፉት ዓላማዎች ጋር አይዛመዱም ያሉ ከመቶ እጅ ከስምንት በላይ ናቸው። በተጨማሪም ተግባሮችና መልመጃዎች ተገቢ ማመሳከሪያ የላቸውም ያሉ ከመቶእጅ ከሃያ ሰባት በላይ ናቸው።

ተግባሮችና መልመጃዎች ፈጠራን አያበረታቱም በማለት ያመለከቱት ከመቶ እጅ ከሃያ ሰባት በላይ ናቸው። በተጨማሪም በበቂ ሁኔታ አለቀረቡም ያሉት ከመቶ እጅ ከሃያ አምስት በላይ ይሆናሉ። በመጁዩሉ ውስጥ የተደራጁት ተግባሮችና መልመጃዎች የግል ጥረት አያበረታቱም ያሉት ከመቶ እጅ ከአስር በላይ ናቸው። እንዲሁም በመተባበር ለመማር አያስችሉም ያሉት ከመቶ እጅ ከያ አምስት በላይ ናቸው።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ሞጅዩሉ እንደገና መከለስ እንዳለበት ይጠቁማሉ። ስለሆንም ይህን መረጃ መሠረት በማድረግ ሞጁዩሉ ብዙ መስተካከልን የሚሻ ነው ማለት ይቻላል።

የሞጁዩሉን አጠቃላይ ይዘቶች በሚመለከት ተማሪዎች ለቀረቡላቸው መስፈርቶች የሰጡትን ደረጃ እንደሚከተለው እንመለከታለን፣

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ አሥራ አምስት፣ የይዘቶች ደረጃ መለያ

| ዓይነት/Item | በ2000 ዓ.ም. በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች | | | | የቀድሞ ተማሪዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| የዓላማ ግልጽነት | 31.39 | 36.09 | 26.74 | 1.2 | 31.25 | 40.63 | 28.13 | __ |
| የቋንቋ ግልጽነት | 26.74 | 36.04 | 37.21 | __ | 40.63 | 43.75 | 15.63 | __ |
| የይዘት ግልጽነት | 23.26 | 32.56 | 34.88 | 3.49 | 18.75 | 43.75 | 37.50 | __ |
| የልዩ ልዩ መግለጫዎች ግልጽነት | 18.60 | 27.91 | 31.39 | 10.47 | 9.38 | 18.75 | 59.38 | 6.25 |
| የሂደት መከታተያ መልመጃዎች ተገቢነት | 26.74 | 44.19 | 34.88 | 2.33 | 28.13 | 25 | 37.50 | 3.13 |
| የማመሳከሪያ ምላሾች ተገቢነት | 22.09 | 34.88 | 31.39 | 10.47 | 28.13 | 31.25 | 21.88 | 9.38 |

መግለጫ፣ 4=እጅግ በጣም ጥሩ

3=በጣም ጥሩ

2=ጥሩ

1=ደካማ

ማስገንዘቢያ፣ ውጤቱ የተገለጸው በመቶኛ ስሌት ነው።

ከሠንጠረዥ አሥራምስት እንደምንረዳው ሞጁዩሉ በአብዛኛው ጠንካራ ጎኖች እን ዳሉት ያሳያል። ይህም የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት የሚያነሳሳ መሆኑ ይታመናል።

ሠንጠረዡ የትኞቹን ጉዳዩች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይጠቁማል። በቀድሞው ተማሪዎችም ይሁን አሁን በ2000 ዓ.ም. በመማር ላይ ይሉት የቋንቋን ግልጽነት በደካማነት አልጠቆሙም። የዓላማ ግልጽነትን በደካማነት የጠቆሙት ከመቶ እጅ 1.2 የሚሆኑ የ2000 ዓ.ም. ተማሪዎች ናቸው። የይዘት ግልጽነትን በደካማነት የጠቆሙ ከመቶ እጅ 3.49 የሚሆኑ የ2000 ዓ.ም. ተማሪዎች ናቸው።

የሂደት መከታተያ መልመጃዎችን ተገቢነት፣ የልዩ ልዩ መግለጫዎችን ግልጽነትና የማመሳከሪያ ምላሾችን ተገቢነት በደካማነት የጠቆሙት የ2000 ዓ.ም. ተማሪዎች በቅደም ተከተል ከመቶ እጅ 2.33፣ 10.47፣10.47 በተጨማሪም የቀድሞ ተማሪዎች 3.13፣6.25፣9.38 የሚሆኑት ናቸው።

ከዚህም የምንረዳው በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በሞጁዩሉ ውስጥ በተደራጁ የማመሳከሪያ

ምላሾች፣ ልዩ ልዩ መግለጫዎች እና ይዘቶች ተማሪዎቹ እንደሚቸገሩ ነው፡፡

## 4.3 ከሞጁል አዘጋጆች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ አሥራ ስድስት፡- ሞጁዩል አዘገጆች በርቀት ትምህርት ላይ የወሰዱት ሥልጠና

| የሥልጠና ርዕስ | ሥልጠናውን የወሰዱ | ሥልጠና ያልወሰዱ |
|---|---|---|
| | ቁ | ቁ |
| የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት፡፡ | 5 | 2 |
| የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አርታኢነት፡፡ | 4 | 3 |
| የርቀት ትምህርት ፕሮጀክት እርማት እና መጋቢ ምላሽ አሰጣጥ፡፡ | 2 | 5 |
| የርቀት ትምህርት አደረጃጀት እና አስተዳደር፡፡ | 1 | 6 |

ከሠንጠረዥ አሥራ ስድስት እንደምንረዳው የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀትና አርታኢነት ሥልጠና የወሰዱ መምህራን ሥልጠና ካልወሰዱት በቁጥር ይበልጣሉ ፡፡ የርቀት ትምህርት ፕሮጀክት እርማትና መጋቢ ምላሽ አሰጣጥ እንዲሁም የርቀት ትምህርት አደረጃጀትና አስተዳደር ሥልጠና ያልወሰዱት ከወሰዱት በቁጥር ከፍተኛ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ የሞጁዩሉ አዘጋጆች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ስልጠና ቢኖራቸውም ከርቀት ተምህርት መርህ አንጻር ተጨማሪ ሥልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ይታያል፡፡

በተጨማሪም በቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ላይ በጠቆሙት መሠረት ሁሉም መምህራን የርቀት ትምህርት ሞጂዩል ከመደበኛው መማሪያ መጽሐፍ በተለየ መንገድ መዘጋጀት እንዳለበት ያምናሉ፡፡ የሚሰጡትም ምክንያት ተማሪዎች እንደመደበኛ ተማሪዎች ከመምህራን ጋር በተከታታይ ለረዥም ጊዜ የማይገናኙ በመሆናቸው ሊያጡ የሚችሉትን እገዛ ሊያካክስ የሚችል ሞጁዩል ያስፈልጋቸዋል የሚል ነው፡፡ በተጨማሪም መጽሕፍት በበቂ ሁኔታ ማግኘት ስለማይችሉ በመረጃ የበለጸገ ሞጁዩል ያስፈልጋቸዋል፡፡ በሚቸግራቸው ነጥብ ላይ ወቅታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው ስለማይኖር ግልጽና የተብራራ ይዘት ሊዘጋጅላቸው ይገባል የሚል ነው፡፡

ሁሉም መምህራን የሞጁዩሉ ቅርጽና የፊደሎች መጠን በተማሪዎች የመማር ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አለው ብለው ያምናሉ። የሚሰጡትም ምክንያት አብዛኞቹ ተማሪዎች የሚኖሩት መብራት ባልተዘረጋበት የገጠር አካባቢ ነው። የማየት እክል በእድሜ፣ በጉዳት እና በተፈጥሮ ምክንያት ያለባቸው ተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ዓይን የሚያስጨንቅ ጽሑፍ ለንባብ አይገፋፋም። የሚሉ ናቸው።

መምህራኑ ይዘቱ የተንዛዛ፣ ለትምህርቱ ከሚሰጠው የተገደበ ጊዜ አንጻር ሊሸፈን የማይችል ነው ይላሉ። ለዚህም ምክንያቱን ሲገልጹ ከበላይ አካል የገጽ ብዛት ተወስኖ ስለሚሰጥ ለመሙላት ተብሎ ስለሚዘጋጅ ነው የሚል ነው።

በተጨማሪም ሞጁሉ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተወሰኑ ታላሚዎች ላይ በከፊልም ይሁን በሙሉ አለመሞከሩ የመልመጃዎችንም ክብደት ይሁን የይዘት መጨናነቅን ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑን ይጠቁማሉ። ይህም በክላሳ ድርሳኑ መሠረት የርቀት ሞጁዩል አዘጋጀጀት ሂደትን ያልተከተለ መሆኑን ያሳያል።

## 4.4 ከርቀት ትምህርት ክፍል የተሰበሰበ መረጃ

በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ መሠረት ለርቀት ትምህርት የተዘጋጁ ሞጁዩሎችን ሁኔታም ይሁን ሌሎች በተማሪዎች ላይ የሚደርሱ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለመከታተል ለጊዜው በተደራጀ መልኩ የተዘረጋ ነገር የለም።

አንገብጋቢ ሁኔታዎች ካሉም ለጊዜው በወረዳዎች በኩል አስተያየት እንዲሰበሰብ፤ በተጨማሪም ተማሪዎች ለቱቶርያል ወይም ለእገዛ በተለያዩ ጣቢያዎች በሚሰበሰቡበት ጊዜ አስተያየት እንዲሰጡ ይደረጋል የሚል ነው። በክለሳ ድርሳኑ ግን ተማሪዎች የማያቋርጥ ክትትልና እገዛ እንደሚያስፈልጋቸው እንዲሁም የሞጁዩሎችን ጥራት አስመልክቶ መረጃ የሚሰበሰብበትን ሂደት ጨምሮ ጥንቃቄ እንደሚገባው ያሳያል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## 4.5 የተሰበሰቡ መረጃዎች ተዛምዶ

የሞጁዩሉ ተጠቃሚዎች ከሆኑት ተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ በሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ የሚደግፍ ነው። ከሞጁዩሉ አዘጋጆች የተገኘውም መረጃ የሰነድ ፍተሻ ውጤትን የሚያጠናክር ነው። በሞጁዩሉ ቅርጽና በሞጁዩሉ ይዘት አደረጃጀት ዙሪያ በዝርዝር በቀረቡት የትኩረት ነጥቦች ላይ ከፍተኛ መደጋገፍ ይታያል። ከርቀት ትምህርት አስተባባሪ የተገኘውም መረጃ ቢሆን በሞጁዩሉ ላይ ለተጠቆሙት አሉታዊ ሁኔታዎች መንስኤዎችን የሚያመለክት ነው።

ኮሌጅ አማርኛ (Amha-101) የሽፋን ገጹ መርሐግብሩን የሚያስተዋውቅም ሆነ ሌላ ሥዕላዊ መግለጫ የለውም። ውስጣዊ ገጽታውም ቢሆን በአብዛኛው በፊደሎች የተጨናነቀ ነው። ይህንን አስመልክቶ ከተማሪዎቹ በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውም መረጃ የሚያረጋግጠው ሞጁዩሉ አብዛኞቹን ተማሪዎች ለንባብ እንደማይገፋፋቸው ነው።

ማስታወሻ ለመያዝም ይሁን ለመልስ መስጫ የተተዉ ቦታዎች አነስተኛ መሆን ተማሪዎቹ ብዙ እንዲሰሩ አይገፋፋም። ጎልቶ አይታይ እንጂ በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውም መረጃ ይህንን ያረጋግጣል። በተጨማሪም አንዳንድ ምልክቶች በይዘቱ ውስጥ ያላቸው አስፋፈር ወጥነት የለውም። ይህንን በሚመለከት ጥቂት ይሁኑ እንጂ ተማሪዎቹም ጠቁመዋል።

የዓላማዎች ዓመላካች መሆን፣ የተግባሮችና መልመጃዎች በአጭር ርቀት እና በበቂ ሁኔታ በየይዘቱ መደራጀት እንዲሁም የዓላማ፣ የይዘትና የመልመጃዎች መዛመድ የሞጁዩሉ ጠንካራ ጎን ነው። የጽሑፍ መጠይቁም እነዚህ ሁኔታዎች ተማሪዎቹን እንዳገዟቸው ያመለክታል። በሰነድ ፍተሻም ይሁን በጽሑፍ መጠይቆቹ ምላሾች፣ በደካማ ጎነንነት ለተጠቆሙ የሞጁዩሉ ክፍሎች መንስኤው አዘጋጆች በመስኩ በቂ ስልጠና ያልወሰዱ በመሆኑ የተፈጠረ ክፍተት እንደሆነ ከቃለመጠይቅ የተገኘውም መረጃ ያመለክታል።

ተማሪዎቹ፣ እንደመደበኛው መርሐግብር ተማሪዎች የጎደላቸውን ከመምህራቸውና ከተጨማሪ ማጣቀሻ መጻሕፍት የሚያካክሱበት ሁኔታ አናሳ በመሆኑ በደካማነት የተጠቆሙት የሞጁዩሉ ይዘቶች በተለያየ መንገድ መስተካከል እንዳለባቸው መረጃው ያሳያል።

ባጠቃላይ በሁሉም መንገድ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተደጋጋፊነት ያላቸውና የሰነድ ፍተሻውን ውጤት አስተማማኝነት ያረጋገጡ ናቸው።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ክፍል አምስት
# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

ጥናቱ በዋናነት በደብረብሃን መምህራን ትምህርት ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ለርቀት መርሐግብር የተዘጋጀውን ‹‹ኮሌጅ አማርኛ›› ከርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት አንጻር ትኩረት የተሰጣቸውን የሞጁዩሉ ክፍሎች የቅርጽና የይዘት አደረጃጀት ፍተሻ የማድረግ እና ለሚገኙ ችግሮች ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ የመፍትሔ ሐሳቦችን በመጠቆም ትምህርቱ ውጤታማና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

ይህ ጥናት ገላጭ የምርምር ዘዴን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ቀደም ሲል የተጠቆሙትን የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ጠቃሚ ናቸው የተባሉ በሀገር ውስጥም ይሁን በውጪ ሀገር የተዘጋጁ ጽሑፎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ የተዘጋጀው ‹‹ኮሌጅ አማርኛ (Amha — 101) የርቀት ትምህርት ሞጁዩል፣ በኮሌጁ ትምህርታቸውን በርቀት የተከታተሉ የቀድሞ ተማሪዎች እና አሁን በ2000 ዓ.ም. በመከታተል ላይ ያሉ ተማሪዎች፣ ሞጁዩሉን ያዘጋጁ እና በተዘረጋላቸው የቱቶሪያል መርሐግብር መሠረት ለርቀት ተማሪዎች እገዛ የሚሰጡ መምህራን እንዲሁም በኮሌጁ የርቀት ትምህርት መርሐግብር አስተባባሪዎች ለጥናቱ ቀዳሚ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል፡፡

በተጨማሪም የሰነድ ፍተሻ፣ የጽሑፍ መጠይቅ እና ቃለመጠይቅ ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት በሥራ ላይ ውለዋል፡፡

በ2000 ዓ.ም. ትምህርታቸውን በርቀት በመከታተል ላይ ላሉ የርቀት ተማሪዎች ከተሰራጩ 100 የጽሑፍ መጠይቆች ውስጥ 86 (86%) እንዲሁም ለቀድሞ ተማሪዎች ከተሰራጩ 40 የጽሑፍ መጠይቆች ውስጥ 32 (80%) ተሞልተው ተመልሰዋል፡፡ አንድ የርቀት ትምህርት አስተባባሪ ለቃለመጠይቅ ተባብረዋል፡፡

በሰነድ ፍተሻ፣ በጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተቀናጅተው ሲተነተኑ በዚሁ ጥናት የተነሱ መሠረታዊ ጥያቄዎች አዎንታዊም አሉታዊም ምላሽ አግኝተዋል፡፡

በዚህም መሠረት የሚከተሉት ነጥቦች እንደ ዋና ዋና ግኝት ቀርበዋል፤

1. በመጀመሪያ ጊዜ ለርቀት ተማሪዎች የተሰራጨው ሞጁዩል የፊደሎች መጠን እጅግ አናሳ በመሆኑ ለንባብ አመቺ አልነበሩም፣

2. በሞጁዩሉ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ መመሪያዎች እና ምልክቶች አመላካች እና አጋዥ ሆነው ተገኝተዋል፤ ይሁን እንጂ በክፍል አንድ፣ ገጽ 17 ‹‹የቃላት ምንነትና አመሠራረት" የሚለውን ርዕስ መሠረት በማድረግ የተሰጠው ‹‹ተግባር ሁለት" ምልክት የለውም፤ በምልክቶች መፍቻ ላይ የተጠቆመው የቁልፍ ምልክት "ተግባራትን" አያመለክትም፣

3. በሞጁዩሉ ውስጥ በየይዘቱ የተነደፉት ዓላማዎች ግልጽና ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የባሕርይ ለውጥ ወይም ዕውቀት፣ክህሎትና አመለካከት የሚጠቁሙ ናቸው፣

4. የተነደፉት ዓላማዎች በአብዛኛው ከይዘቶች፣ ከተግባሮች እና ከመልመጃዎች ጋር የተዛመዱ ናቸው፣

5. ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ሌሎች ማጣቀሻ መጻሕፍትን ማንበብ የሚጠይቁ ተግባሮች በሞጁዩሉ ውስጥ ተካተዋል፡፡(ለምሳሌ፣የንግግር ድምጾችን በሚመለከት የቀረቡ ተግባሮች) በተለይ ማጣቀሻ መጻሕፍቱ በማይገኙበት የገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎች ተግባሮቹን ለመስራት ተቸግረዋል፤ በመሆኑም ተማሪዎች የእገዛ ጊዜያትን ብቻ በመጠበቅ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ፣

6. ተግባሮች እና መልመጃዎች በአጭር ርቀት የተደራጁ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በበቂ ሁኔታ መቅረባቸው የተማሪዎችን በራስ የመማር ሂደት አግዟል፣

7. ሞጁዩሉን ለማሻሻልና የሚፈለገውን የትምህርት ጥራት ለማምጣት ተማሪዎች አስተያየት የሚሰጡበት የተደራጀ የአሠራር ሂደት የለም፣



ADDIS ABABA UNIVERSITY
I.E.R LIBRARY

8. አንዳንድ ተግባሮች ምላሻቸው የቀደመ ዕውቀትን የሚጠይቅ እንጂ ከሞጁይሉ ውስጥ የሚገኝ አይደለም፣

9. ሞጁዩሉ ከሌሎች ልዩ ልዩ ሚዲያዎች ጋር የተቀናጀ አይደለም።

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች

የርቀት ተማሪዎች በአጠቃላይ መማር ማስተማሩ ሂደት የተለያዩ መሰናክሎች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ። ችግሮቻቸው በመማሪያ ሞጁዩሎች ላይ፣ የእገዛ ጊዜያትንና ሁኔታን የሚመለከት የተጨማሪ ሚዲያዎችን አደረጃጀት በሚመለከት፣ በሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ፣ ወ.ዘ.ተ. ሊሆን ይችላል።

በመስኩ የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት ይቻል ዘንድ አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደቱን ሥርዓት ባለው ሁኔታ በመከታተል ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው።

በመማር-ማስተማር ሚዲያ ሥር በሚካተተው፣ በገባ-ወጣ-ገባ መርሐግብርም ጭምር በማገልገል ላይ ባለው በኮሌጅ አማርኛ /Amha-101/ የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የተደረገውን ጥናትና የተረጋገጡበትን ግኝቶች መነሻ በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ተጠቁመዋል፤

- ሞጁዩሉ በአማዛኙ ለርቀት ተማሪዎች አመች በሆነ መንገድ የተደራጀ ነው። የበለጠ ውጤታማ እና ትምህርቱ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ይቻል ዘንድ፣ ግልጽነት ይጎላቸዋል፣ ማብራሪያ የላቸውም፣ በሞጁዩሉ ምላሽ አያገኙም የተባሉ ይዘቶች እንዲሁም ሌሎች የህትመት ስህተቶች የሚለቀሙበት ቅጽ ተዘጋጅቶ ለተማሪዎች ቢሰራጭ፣

- ሞጁዩሉ አዋጭነቱ ተጠንቶ ከሌሎች ሚዲያዎች ጋር ተቀናጅቶ ቢደራጅ፣

- ለወደፊት በሚሰራጩ የርቀት ትምህርት ሞጁዩሉ ውስጥ የአስተያየት መሰብሰቢያ ቅጾች በየይዘቱ ተደራጅተው ቢካተቱ፣

- የሚሰበሰቡ ማስተካከያዎችን የማደራጀትና ሞጁዩሎች የሚከለስበት ሥርዓት በኮሌጁ ቢዘረጋ፣

- አንድ የትምህርት ወቅት ወይም ዑደት ሲጠናቀቅ ስለአጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደቱ የተጠናከረ መረጃ ሊያስገኝ የሚችል ጥናት ቢደረግ፣

- ወደፊት የሚዘጋጁ ሞጁዩሎች በመስኩ ባለሞያዎችን ያካተቱ ቢሆኑ፣

- ለርቀት መርሐግብር የተዘጋጁ የሌሎች ሞጁዩሎችም አደረጃጀት ቢፈተሽና ጠንካራና ደካማ ጐናቸው ቢለይ፣

የሚሉት ናቸው።

በአገራችን የርቀት ትምህርት እየተስፋፋ ይገኛል፤ በመሆኑም ትምህርቱ ጥራትን የጠበቀ እንዲሆን የመስኩ ባለሞያዎችን ይፈልጋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ትምህርት ሚኒስተር ትኩረት መስጠት ይኖርበታል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY SGS LIBRARY

# ዋቢ ጽሑፎች


ደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ (1998):: ኮሌጅ አማርኛ:: (ያልታተመ)::

ጌታቸው ቀለሙና ሌሎች (1983):: የርቀት ትምህርት ፖሊሲ ጥናት:: (ያልታተመ)::

Amare Bizuneh (2006). "The Role of M.Ed Distance Education Program in Building the Capacity of the Ministry of Education." The Ethiopian Journal of Higher Education. Vol. III. No. 2 pp.72-73.

Bates, A.W.(1995) Technology,Open Learning and Dietance Education. London: Routledge.

Best, J. and Khan, J. (1993). Research in Education. 7th ed. New Delhi: prentice Hall.

Cunnings worth, A. (1995) . Choosing Your Coursebook. Oxford: Heinmann.

_________ (1984). Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials. Oxford: Heinmann.

Cyrs, Thomas E.(ed.) (1997). Teaching and Learning at a Distance: What It Takes to Effectively Design, Deliver, and Evaluate Programs. Sanfrancisco : Jossey-Bass Publishers.

Ejeta Negeri (2005). A Study on the Effectiveness of the Implementation of Distance Education (Project 17.000) for the Second Cycle Primary School Teachers: Specific to English Language Courses. A.A.U MA. Thesis.

EMA (1999). Handbook for Designing and Writing Distance Education Materials. Addis Ababa (Unpublished).

Grant, N. (1987). Making the Most of Your Text Book. New York: Longman Inc.

Harry, K. Jhon, M. & Keegan, D. (Ed) (1993). Distance Education: New Perspective. New Fetter lane: Rythedge Flamer.

Hawas, G.R. (1982). The Concise Dictionary of Education. New York: Hudson Group.

Holmberg, B. (1989). Theory and Practice of Distance Education. New Fetter Lane: Routledge.

Judith, C. (1994). Program Evaluation and Quality: A Comprehensive Guide to Setting up an Evaluation System. Bolden: Biddles Ltd.

Khan, A. W. and McWillams P.(1998) "Application of Interactive Technologies in Open and Distance Learning; An Overview" Indian Journal of Open Learning. 7(1) pp 7-21.

Keegan, D. (Ed.) (1993). Theoretical Principles of Distance Education. North York shire J & L composition Ltd.

________ (1996). Foundations of Distance Education. London: Routeledge.

LockwooD, F. (1998). The Design and Production of Self-instructional Materials. London: Biddles Ltd.

Manidi, S. and R.M. (1984). Curriculum Development and Educational Technology. New Delhi: Streling Publishers.

McDonugh, J. and Christopher Show (1994). Materials and Methods in ELT: Teacher's Guide. Oxford: Blackwell Publishers.

Melton, R. (2002). Planning and Developing Open and Distance Learning: A Quality Assurance Approach. Boldon: Wearest Ltd.

Perraton, H. (ed.) (1993). Distance Educaiton for Teachere Training. New York: Routledge Falmer.

Prasad,V.S (1999). Quality Assurance in Open and Distance Learning Materials, Perosnal Communication. New Delhi: Indira Gandhi Nationa Open University.

Richardson, J. G. And George W. Bostick Developing Learning Modules. (http: // WWW. ces.ncsu.edu/About CES/Factsheet/develophtm/)

Rowntree, D (1992). Exploring Open and Distance Learning. Lindon: Kogan Page.

________ (1990). Teaching Throught Self-inetruction. New York: Nichola Publishing Campany.

Sherry,L. (1996) "Issuse in Distance Learning" nternational Journal of Educational Tele Communacation. 1(4) pp337-365.

STRIDE (2001). Communication Technology for Distance Education: Media in Distance Education. New Delhi: Akashedeep Printers.

________ (2001). Design and Development of Self-learning Print Materials: Factors in the Design of Print Materials. New Delhi: Repro offset printer.

________ (2001). Design and Development of Self-learning Print Materials: Preparation of Texts. New Delhi: Repro offset printer.

________ (2001). Design and Development of Self-learning Print Materials: Principles of Text Design. New Delhi: Repro offset printer.

________ (2001). Design of Distance Teaching Materials: A Review. New Delhi: Repro offset printer.

________ (2000). Growth and Philosophy of Distance Education: Growth and Innovations: Glimpses.1, New Delhi: Bery Art Press.

________ (2000). Growth and Philosophy of Distance Education: Philosophical Foundation. New Delhi: Bery Art press.

________ (2001). Management of Distance Education: Planning and Management of Distance Education. New Delhi: Akashdeep Pringers.

________ (2001). Preparation of Study Materials: Operational Aspects. New Delhi: Repro offset Printer.

Taylor,J.(1998) "Flexible Delivery: The Globalization of Life Long Learning" Indian Jornal of Open Learning. 7(1) pp 55-65.

Woodley,Alan, and Adran Kikiwood(1988) "Evaluation Distance Leaning" In J. Jenkins.ed.,Common Wealth Co-operation in Open Learning; Back Groud papers. London: Common wealth Sceretariat,pp291-98.

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

## የምልክቶች መፍቻ



ይህች ምልክት የምትጠቁመው የሞጁዩሉ ወይም የክፍሉ መግቢያ መሆኑን ነው።



ይህች ምልክት የምትጠቁመው የመልመጃ ጥያቄዎች መሆናቸውን ነው።



ይህች ምልክት የምትጠቁመው የራስ መገምገሚያ ጥያቄዎች መሆናቸውን ነው።



ይህች ምልክት የምትጠቁመው የማገናዘቢያ ጥያቄዎች መሆናቸውን ነው።



ይህች ምልክት የምትጠቁመው የግባራትና የራስ መገምገሚያ መልሶች መሆናቸውን ነው።



ይህች ምልክት የምትጠቁመው የተግባር ጥያቄዎች መሆናቸውን ነው።

# አባሪ ሁለት

## ክፍል አንድ፡- የቃላት ምንነትና አመሠራረት

### መግቢያ

የሰው ልጅ የንግግር ቋንቋ ያለ ቃላት ይናራል ብሎ ማሰብ አይቻልም (ሰለሞን ሐለፎም 1997፡1)። በሰዎች መካከል በቋንቋ አማካይነት የሚደረገን የሀሳብ ልውውጥም እንዲሁ። በመሆኑም ቃላት፣ ከቋንቋ አካላት መካከል አንደ አንዱ ከመቆጠራቸውም በላይ፣ በሰዎች የተግባቦት (communication) ሂደት ወሳኝ ሚናም አላቸው። ስለሆነም፣ ስለ ቃላት ምንነትና አመሠራረት ማወቅ ጠቀሜታው የጉላ ነው።

ውድ የርቀት ትምህርት ባልደረቦቻችን! በዚህም ክፍል በመጀመሪያ በቃላት ምንነት ላይ ያተኮረ ትምህርት ይቀርብላችኋል። በመቀጠልም ስለ ቃላት አመሠራረት የሚያብራራ ትምህርት ይከተላል።

ትምህርቱም፣ በተለያዩ ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች ተደግፎ ይቀርባል። ትምህርቱን የበለጠ ለመረዳትና ግልፅ ለማድረግ የተለያዩ መልመጃዎችና ተግባራት እንዲሁም ማመሳከሪያዎች ተዘጋጅተዋል። ስለዚህ፣ መልመጃዎቹንና የተግበራቱን፣ የማጠናከሪያና የማጠቃለያ ሀሳቦችን ከማንበባችሁ በፊት በጥንቃቄና በትኩረት መሥራት ይኖርባችኋል።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ይህንን ክፍል ከተማራችሁ በኋላ ከእናንተ የሚጠበቀውን የአስተሳሰብና የአሠራር ለውጥ የሚያመለክተው ዓላማ ቀርቦላችኋል። መልካም ንባብ!

### ዓላማ

የዚህን ክፍል ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የቃላትን ምንነት ታብራራላችሁ።
- በንግግር ድምፅና በዘረ ድምፅ መካከል ያለውን ልዩነት ትዘረዝራላችሁ።
- በምእላድና በቃል መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ታስረዳላችሁ።
- ለአዲስ ቃል ምሥረታ መንስኤው ምን እንደሆነ ትገልፃላችሁ።
- የቃላት አመሠራረት ሥርዓቶችን ታብራራላችሁ።

### 1.1. የቃላት ምንነት

በማንኛውም ቋንቋ ቃላት ይገኛሉ። በየቋንቋው የሚገኙት የቃላት ብዛትም እንደ ቋንቋው እድገት ይወሰናል። ባደጉትና በበለፀጉት ቋንቋዎች የሚገኘው የቃላት ብዛት እጅግ በርካታ ሲሆን፣ ባላደጉትና ባልበለፀጉት ቋንቋዎች ደግሞ በመጠኑ ያነሰ የቃላት ክምችት እንዳለ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በየትኛውም ቋንቋ የሚገኙ ቃላት ቁጥራቸው ይብዛም ይነስ ለሚጠቀምባቸው ህብረተሰብ አካባቢውን መግለፅ ያስችላሉ።

ማንኛውም ሰው አካባቢውን የሚገልፀው ወይም ስለ አካባቢው ከሌሎች ጋር ሆኖብ የሚለዋወጠው በቋንቋው የሚኙትን ቃላት እየተጠቀመ መሆኑን ያውቃል። ኗሩ ግን ስለሚጠቀምባቸው ቃላት ምንነት ራሱን የሚጠይቅ ቢኖር እጅግ በጣም ጥቂት ነው።

ውድ የርቀት ትምህርት ባልደረቦቻችን! የከዚህ ቀደም እውቀታችሁን በመጠቀም የሚከተሉትን ከቃላት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች መልሱ።

?

**መልመጃ አንድ**

1. ስለ ቃላት ምንነት የራሳችሁን ብያኔ ስጡ

______________________________

2. ቃላት ከምንና እንዴት እንደሚመሠረቱ አስረዱ።

______________________________

3. በንግግር ድምፅና በዘረ ድምፅ መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ።

______________________________

4. በቃላትና በምእላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለፁ።

______________________________

ለተያቄው መልስ ለመስጠት እንደሞከራችሁ ይገመታል፡፡ ይሁንና እስኪ የሰጣችሁትን መልስ ቀጥሎ ከተሰጠው ግብራሪያ ጋር እያነፃፀራችሁ ለማተናት ሞክሩ፡፡

ግንኙነም ቋንቋ በባህሉ ውስጥ የለውን ግንኙነንም ነገር የመግለፅ ሙሉ ሃይል አለው፡፡ ይሁንና ከባህሉ ውጪ የሆኑ አዳዲስ ፅንሰ ሃሳቦች ወይም ቁሳዊ ስያሜዎች ከሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር በሚደረግ ግሀበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ግንኙነቶች ሳቢያ ቢያጋጥሙት የመግለፅ ገዴታ የለበትም፡፡ ውስትም ገድ የሚሆነው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ ግንኙነቱ እስካለ ድረስም በሂደቱ በርካታ ቃላት ወደ ቋንቋው ሊገቡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በተለያዩ ግሀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ግንኙቶች ምክንያት ተደም ሲል በቋንቋው ውስጥ ያልነበሩና ወደ ቋንቋው በውስት የሚገቡ በቃላት የባእድ ቃላት ይባላሉ፡፡

ውስት የቋንቋ ጤነኛ ባህርይ በመሆኑ ቀድሞም የነበረ፣ ዛሬም ያለና ወደፊትም የሚኖር ነው፡፡ አማርኛ ቋንቋም ከልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተውሶ የራሱ ካደረጋቸው ቃላት ውስጥ ጥቂቶችን ቀጥሎ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

- ሰንጋ፣ ሎሚ፣ ወዘተ -------------ከኦሮምኛ
- ጀበና፣ ሱቅ፣ ሰአት፣ አቡጀዲ፣ ወዘተ ---ከአረብኛ
- ዝግር፣ ጳጳስ፣ መነኩሴ --ወዘተ ---ከግሪክ
- ኮት፣ ሸሚ፣ ወዘተ -----ከፈረንሳይኛ

በተጨማሪም ኮምፒውተር፣ ሲዲ፣ኢንተርኔት፣ ቴሌቪዥን ግሎባላይዜሽን፣ ኤክስቴንሽን የመሳሰሉት ቃላት ዛሬ አማርኛ የራሱ እያደረጋቸው ያሉ ቃላት ናቸው፡፡

(?)

**መልመጃ አስራ ሶስት**

የተከበራችሁ የዚህ ትምህርት ተከታታዮች! የባዕድ ቃላት በኢ-መደበኛነት የተመደቡትን ምክንያት ለማስረዳት ሞክሩ፡፡

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________



ADDIS ABABA UNIVERSITY HLS LIBRARY

ሙከራችሁን ከዚህ ቀጥሎ ከሚቀርበው ግብራሪያ ጋር አዛምዱ፡፡

የባዕድ ቃላትን በንግግርም ይሁን በፅሁፍ ጣልቃ እያስገቡ የመጠቀም ልምድ በአብዛኛቹ የተማሩ የቋንቋው ተጠቃሚዎች ዘንድ አዲስ አይደለም፡፡

ከመደበኛ ድርሰት መርህ አንፃር "ጉራማይሌ" አጠቃቀም ኢ-መደበኛ ነው፡፡ በንግግርም ይሁን በፅሑፍ የመግባባት ሂደት አጠቃቀሙ ከንግግሩ ወይም ከፅሑፉ አላማ፣ ይዘት፣ እንዲሁም ከአድማጩ ወይም አንባቢው ማንነት አንፃር ካልተለየ በስተቀር የመግባባት ሂትን ያደናቅፋል፡፡

አድማጭም ይሁን ተናጋሪው በሚያደርጉት የግል ጭውውት ጣልቃ ለሁሉም የጋራ የሆነ ቃል ቢጠቀሙ የመግባባት ሂደት ላያደናቅፍ ይችላል፡፡ ለብዙሃኑ አድማጭ በሚተላለፍ መደበኛ ውይይት ሂደት ውስጥ ጉራማይሌ ቃላትን መጠቀም ኢ-መደበኛ አጠቃቀም ይሆናል፡፡ በመገናኛ ብዙሃን በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ለብዙሃኑ አድማጭ በሚተላፉ ቃለመጠይቆች ውስጥ "ጉራማይሌ" ቃላት መጠቀም የሀሳብ መምታታትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

አንዳንድ በንግግር ሂደት የተለመድ ቃላት በመደበኛ ድርሰት ውስጥም ሲገቡ ይታያል፡፡

ለምሳሌ፡-

1. የኤለመንተሪ ተማሪ እያለሁ. . .
2. ማትሪክ ስፈተን. . .

በምሳሌ ቁጥር 1 የተገለፀው የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ

2. የተገለፀው የሁለተኛ ደረጃን መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ስፈተን" ሲባል ይችላል፡፡

ከምሳሌው የምንረዳው ፅንሰ-ሀሳቡን በቋንቋው መፍታት ከተቻለ በቋንቋው አቻ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ የባዕድ ቃላት አጠቃቅምም ኢ-መደበኛ የሚሆነው ቋንቋው የሚገልፀው ቃል እያለ የባዕድ ቃልን እየተኩ ሲጠቀሙ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቆሙትን አይነት "ጉራማይሌ" አጠቃቀሞች በድርሰት ውስጥ እንዳይገቡ መጠንቀቅ ተገቢ ነው፤ ነገር ግን አቻ ፍቺ የሌላቸውን ቃላት መጠቀም የማይቀር ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ኢንተርኔት፣ ኮምፒውተር ወዘተ የመሳሰሉት በቋንቋው አቻ ስለሌላቸው በመደበኛ ድርሰት እንዳለ መግባታቸው የግድ ነው፡፡



56

ቃል መርጦ መጠቀም የሚቻለው የቃላትን ተለዋዋጭ ባህርይ መገንዘብ ሲቻል ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ቃል በፍቺ ለተሳካ የቃላት ምርጫ የቃላትን በእውዳዊ ፍቺ የመለዋወጥ ባህርይ፤ የተመሳሳይ ቃላትን በፍቺ መለያየት፣ የቃላትን አግሬያዊና ፍካሬያዊ የፍቺ ልዩነት፣ የፈሊጣዊ ቃላትን ምንነትና አጠቃቀም፣ ከዘመን ወይም ወቅት ጋር የቃላትን ፍቺ መቀያየርና የተሰለቹ ቃላትን ባህርይ በወጉ መረዳትና ትኩረት መስጠት ይርበታል፡፡ እነዚህንም መሰረታዊ ነጥቦች ቀጥሎ በዝርዝር ለመመልከት እንሞክር፡፡

### 3.3.1. ቤእውዳዊ /አገባባዊ/ ፍቺ

አንድ ቃል በአረፍተ ነገር ውስጥ ገብቶ፣ በቁሙ ይኖረው ከነበረው ትርጉም/ፍቺ/ የተለየ ትርጉም /ፍቺ/ ሲሰጥ የቃላትን እውዳዊ ፍቺ ይባላል፡፡ ምክንያቱም ቃል ወኪል በመሆን ለበርካታ የተለያዩ እሳቤዎች ድርብርብ ውክልና ሊኖረው ስለሚችል ነው፡፡ ለዚህም አንድ ቃል በቁሙ ወይም በቀጥተኛ ፍቺው ከሚወክለው ነገር በተጨማሪ ያለው ውክልና ገለፃ የሚሆነው ቃሉን በተለያዩ አገባቦች ተጠቅሞ መለየት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ቃላት በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ገብተው የተለያዩ ፍቺዎችን የመግለፅ ባህርይ ስለሚኖራቸው ይህንን ባህርያቸውን በአግባቡ መረዳት ተገቢውን ቃል ለተገቢው አገባብ መርጦ የመጠቀምን ችሎታ ያዳብራል፡፡ ይኸውም ቃሉን ለየትኛው ፍቺና በየትኛው አገባብ መጠቀም እንደሚገባ ለይቶ ማወቅ እና መገልገል ካልተቻለ የመልእክት አሻሚነትን፣ መደብዘዝን ወይም ጨርሶ መፋለስን ሊያስከትል ይችላል፡፡

አንድ ቃል በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ገብቶ ፍቺውን እንዴት እንደሚለዋወጥ ቀጥሎ በተሰጠው ምሳሌ እንመልከት፡፡

ምሳሌ፡- በላ

1. ካሳ ምሳውን በላ፡፡ /ተመገበ/
2. ካሳ የተሰጠውን አደራ በላ፡፡ /ካደ/
3. ካሳ እቁብ በላ፡፡ /ደረሰው፣ ወሰደ/
4. አለሙና ተዋበ የተወራረዱበትን ተዋበ በላ፡፡ /አሸነፈ/
5. መሬቱን ውሃ በላው፡፡ /ሸረሸረው/
6. ከለፈው ሳምንት ወዲህ ልጁን ምን እንደበላው አልታወቀም፡፡ /የትእንዳለ/





ተግባር አስራ ሁለት

የተወደዳችሁ የዚህ ትምህርት ተከታታዮች! ስለቃላት እውዳዊ ፍቺ መገንዘባችሁን ለማረጋገጥ ትችሉ ዘንድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትእዛዛቸው መሰረት ስሩ፡፡

UNIVERSITY

መመሪያ 1. ከዚህ በታች "ቀመሰ፡ በሚለው ቃል የተለያዩ አረፍተ ነገሮች ተመስርተዋል፡፡ በእያንዳንድ

አረፍተ ነገር ውስጥ ቃሉ የሚሰጠውን እውዳዊ ፍቺ ለይታችሁፃፉ ፡፡

1. አለሙ ወጡን ቀመሰ፡፡
2. አለሙ ጥፊ ቀመሰ፡፡
3. አለሙ መከራ ቀመሰ፡፡
4. አለው ስድብ ቀመሰ፡፡
5. አለሙ መድሀኒት ቀመሰ፡፡
6. አለሙ አፈር ቀመሰ፡፡

መመሪያ 2. የሚከተሉት ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ገብተው የሚኖራቸውን የተያዩ ፍቺዎች ለእያንዳንድ ቃል የቻላችሁትን ያህል አረፍተ ነገሮች በመስራት አሳዩ፡፡

1. ፈረሰ
2. ወደቀ
3. ሞተ
4. ጣለ
5. ወረደ

### 3.3.2. በተመሳሳይ ፍቺ

መልመጃ አስራ ስምንት

የተለያዩ መልመጃዎችን ስትሰሩ የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ በሚመለከት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ የተለያዩ መልመጃዎችን እያዘጋጀችሁ ቆይታችኋል፡፡ አሁን ባላችሁበት ደረጃ ደግሞ ለተማሪዎቻችሁ የተለያዩ ምሳሌ በመስጠት ተለማምዳላችሁ፡፡ ለመሆኑ የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ማለት ምን ማለት ነው? አስረዱ፡፡

_______________________________________________

_______________________________________________

እድምቶ ለመግለፅ የሚገባው ደገም ገላጭ ይባላል፡፡ በተነፃፃሪዎቹ መካከል መኖር ያለበት የጋራ ባህሪ ደገሞ ሰበበ ንፅፅር ተብሎ ይጠናል፡፡ በአንድ አነፃፃሪ ዘይቤ ተገላጩና ገላጩ በሰበበ ንፅፅራቸው ተቆራኝተው ምስል የሚፈጥሩትና እንጋገሩ ግብ መቼ የሚሆነው ሁለቱም በግልፅ የታቁ እንደሆን ነው፡፡ /ዘሪሁን አስፋው፡1992/


አነፃፃሪ ዘይቤ ሁለት ነገሮችን፣ ሁነቶችን ወዘተ የሚያነፃጸርበት፣ የሚያወዳድርበት የማነፃፀሪያውና የማወዳደሪያ ቃላት /ሐረጋት/ አሉት፡፡ ለምሳሌ እንደ ፣ ያህላል፣ ይመስላል፣ ከ . . . ጋር ይወዳደራል የመሳሰሉ ቃላትንና ሐረጋትን/ በግልፅ ይጠቀማል፡፡

፡፡ በአነፃፃሪ ዘይቤ ውስጥ ገላጭና ተገላጭ የሚባሉት በሚከተለው ምሳሌ ገልፅ በሆነ መልኩ ቀርበውላችኋል፡፡

ምሳሌ፡- አበበ አንበሳ ይመስል ስጋ ይወዳል፡፡

በቀረበው ምሳሌ ውስጥ ገላጩ አንበሳ ሲሆን ተገላጩ አበበ ነው ሰበበ ንፅፅሩ ስጋ መውደድ ሲሆን ማነፃፀሪያው ደገሞ ይመስል፡፡ የሚለው ነው፡፡ ይህም በስእላዊ መግለጫ እንደሚከተለው ሊቀርብ ይችላል፡፡

አበበ አንበሳ ይመስል ስጋ ይወዳል







58

ከላይ እንደተከታተላችሁት ተነፃፃሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ከተለያዩ ጉራዎች የመጡ /የተገኙ/ ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ ግን ከአንድ ጉራ የሆኑ ነገሮችም ተነፃፅረው ለሐሳብ መገለጫነት ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡ ሆኖም ምስል ሊፈጥር የሚችለው ተነፃፃሪዎቹ በየጉራቸው የተለያዩ ባህሪያትን የሚያሳዩና በተለየ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ ለዚህም የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሄለን እንደ ሙሽራ ደምቃለች




ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

ተግባር አስራ ሰባት

በሚከተሉት አነፃፃሪ ዘይቤዎች ውስጥ ገላጭ ተገላጭ፣ ሰበበ ንፅፅርና ማነፃፀሪያ ቃሉን በመለየት አውጡ፡፡

1. ዘነበች ከተቀመጠችበት እንደኳስ ነጥራ ተነሳች፡፡
2. ልጃገረድ ይመስል ይሽኮረመማል፡፡
3. ሲበላ እንደ ጅብ ነው፡፡
4. አልማዝ የፅጌረዳ አበባ ትመስላለች፡፡

ውድ የርቀት ትምህርት ባልደረቦቻችን! በአነፃፃሪ ዘይቤ ውስጥ የሚነፃፀሩ ነገሮች ከተለያዩ ጉራዎች የተገኙ የተለያየ ባህሪያት ያላቸው ነገሮች ይሁኑ እንጂ አልፎ አልፎ በተመሳሳይ ጉራም ያሉ ነገሮች የሚነፃፀሩበት ሁኔታም አለ፡፡ አነፃፃሪ ዘይቤ ምን ጊዜም ቢሆን አይቀሬ የሆኑ ሁለት አካላት አሉት፡፡ እነሱም ገለጭና ተገላጭ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሁለቱን አካላት የሚያነፃፅሩ፣ የሚወዳድሩ ቃላት/ሐረጎች/ ሊኖሩት ይገባል፡፡

## ክፍል አምስት፡- አረፍተ ነገር

**መግቢያ**

በንግግርም ሆነ በፅሁፍ የተቃናና የተስተካከለ የሀሳብ ፍሰትን የተከተለ መልእክት ለማስተላለፍ የተሟላ ሀሳብን ወይም ስሜትን የሚገልፅ አረፍተ ነገር መገንባት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ያልተዛባ ወይም የሀሳብ ምሉዕነት ያልጐደለው ንግግር/ፅሁፍ ለማቅረብ ስለአረፍተ ነገር ምንነት፣ ባህሪያትና የአገነባብ ስልቶች መለየት ስለሚያስፈልግ በሚቀርቡት ተግባራዊ ልምምዶች ላይ በትጋት መስራት ተገቢ ነው፡፡

### አላማ

ከዚህ ክፍል በኋላ ፡-

- የአረፍተ ነገርን ምንነት ትገነዘባላችሁ፡፡
- መሠረታዊ የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ትለያላችሁ፡፡
- የአረፍተ ነገር ማስፋፊያ ስልቶችን ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገርን ታስፋፋላችሁ፡፡
- የተለያዩ የአረፍተ ነገር አይነቶችን ትረዳላችሁ፡፡

## 5.1. የአረፍተ ነገር ምንነት

**መልመጃ አንድ**

ሀ. አረፍተ ነገር ምንድን ነው? የምታስታውሷቸው ነጥቦች ለመጥቀስ ሞክሩ፡፡

______________________________

______________________________

ለ. በድምፅ፣ በቃል፣ በሀረግና በአረፍተ ነገር መካከል ያለው አንድነትና ልዩነትስ ምንድነው? አስረዱ፡፡

______________________________

______________________________

______________________________



የተወደዳችሁ የዚህ ትምህርት ተከታታዮች! ከላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞከራችሁ? ጥሩ ነው! እስኪ መልሳችሁን ቀጥሎ ከተሰጠው ማብራሪያ ጋር ለማመሳከር ሞክሩ፡፡

በየትኛውም ቋንቋ የሚገኙ የንግግር ድምፆች በስርአት ተቀናጅተው ትርጉም አዘል የሆነ ቃልን ይመሠረታሉ፡፡ ትርጉም አዘል ቃላት ደግሞ የቋንቋው ስርአት በሚፈቅደው ቅደም ተከተል ተቀናጅተው ሀረግን ከፍ ሲልም አረፍተ ነገርን ይመሰርታሉ፡፡ አረፍተ ነገር ሙሉ ሀሳብን ሊገልፅ የሚችል የቃላት ስብስብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ምሳሌ ሀ/ ድምፅ -ብ፣ ክ፣ ጥ፣ ቅ፣ ች ወዘተ

ለ/ ቃል - ተማረ፣ አጠና፣ ሰራ፣ በሬ፣ ወንዝ፣ ወዘተ

ሐ/ ሀረግ - እየተማረ፣ የሚያጠና ልጅ፣

መ/ አረፍተ ነገር - ልጁ መጣ፡፡

- ገበሬው ታታሪ ሰራተኛ ነው፡፡
- የተማረ ዜጋ አገርን ያኮራል፡፡
- ጠንክሮ ያጠና ተማሪ ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ ያልፋል፡፡

ከላይ በተሰጡት ምሳሌዎችውስጥ በፊደል ተራ "ሀ" ላይ የተመለከቱትና ሌሎች የንግግር ድምፆች በራሳቸው ትርጉም አልባ ናቸው፡፡ይሁን እንጂ እነዚህን ትርጉም አልባ ድምጾች በቅደም ተከተል እያቀናጀን ቃል መስርተን ልንጠቀምባቸው እንችላለን፡፡ ቃላት ደግሞ በትርጉም ወይም በፍቺ የሚታወቅን አንድ ነገር፣ ሀሳብ ወይም ሁኔታ ያመለክታሉ፡፡ ቃላት አንድን ፅንሰ ሀሳብ ከመጠቆም ውጪ የሰፋ መልእክት ሊያስተላልፉ አይችሉም፡፡ ሰፊ ሀሳብን ለማመልከት አንድ ቃል ከሌላ ቃል ጋር አብሮ በመሰለፍ መቀናጀት አለበት፡፡ ለምሳሌ "ሰራተኛ" የሚለው ቃል "ገበሬ" ከሚለው ሌላ ቃል ጋር ተቀናጅቶ ሲገባ "ሰራተኛ ገበሬ" የሚለውን ሀሳብ ይመሠርታል፡፡ ሁለት ትርጉም ያላቸው ቃላት በመሆናቸው አንድ ቃል ብቻውን ከሚሰጠው ሀሳብ የሰፋ መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡ ነገር ግን የተላለፈው ሀሳብ አሁንም የተሟላ አይሆንም፡፡ "ሰራተኛ ገበሬ" የሚለው የገበሬውን ማንነት /ምንነት፣ የት እንደሚኖር፣ በምን አይነት የግብርና ዘርፍ ላይ እንደተሠማራ ወዘተ. አያመለክትም፡፡ አረፍተ ነገር ደረጃ ከደረሰ ግን ሙሉ ሀሳብን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

ምሳሌ፡- አቶ አየለ በደ/ብርሃን አካባቢ ከሚታወቁት ታታሪ የንብ አርቢ ገበሬዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የገበሬውን ማንነት፣ የት እንደሚኖር፣ በየትኛው የግብርና ዘርፍ እንደተሰማራ፣ የአምራችነት ደረጃውን ወዘተ. ያመለክታል፡፡ አረፍተ ነገር እንደሚያስተላልፈው መልእክት ሊሰፋም ሊጠብም ይችላል፡፡

ምሳሌ፡- - አበበ መጣ፡፡



59

ዘይቤው ------------------------------------

የዘይቤው ዓይነት ----------------------------

4. አንድ ቀን ብሬት ድስት ሸክላ ድስትን አለው
እኔን ነው በሁሉም መልክህ የሚመስለው፡፡
/ ከበደ ሚካኤል፣ 1956/

ዘይቤው ---------------------------

የዘይቤው ዓይነት ----------------------------

5. ገንዘብ በረዶ ነው ይከስማል ይጠፋል፡፡
ለፍቅር እንኳር ሌላው ነገር ያልፋል፡፡

ዘይቤው ------------------------------

የዘይቤው ዓይነት -------------------------

6. ሆምሌ ድንጋይ ይዟል ነሐሴ ሰይፍ መዟል
መስከረም ጦር ይዟል ሰው ሊገድሉላችሁ
አትገላገሉም ወይ ያላችሁ ያላችሁ

ዘይቤ-----------------------------------------

የዘይቤው ዓይነት ---------------------------

7. እንደ ሐምሌ ወራት ፊቷ ጨፍን ለብሶ
እንደ መኸር ድርቆሽ ልብሷ ተልከስክሶ
እየኋት ለየኋት እንዲቷን ቀዘባ
ዘንጠፍ ዘና ብላ እንደመስከ አበባ፡፡

ዘይቤ ---------------------------------------------

የዘይቤው ዓይነት -------------------------------

8. እናት አውድማ ናት የተለቀቀለ
ቢበሉ ቢጠጡ አትልም አለቀ፡፡

ዘይቤው ----------------------------------------------

የዘይቤው አይነት ------------------------------------

**መመሪያ ሶስት፡- ከዚህ በታች የቀረቡት በየትኛው የዘይቤ ዓይነት እንደተገለፁ ፃፉ፡፡**

1. የኤሌክትሪክ ብርሃኑም ያፈጣል እንጂ ምንም አያሳይም፡፡ ------------------------------------
2. አለሙ እኔ የምኖረው ያለ ህይወት ነው ማለት ያዘወትረሀል፡፡ ---------------------
3. እንደ ንብ ታታሪ እንደርገብ የዋህ ሁን፡፡---------------------
4. ማልደሽ ስለተነሳሽ አርፍደሽ ደረስሽ፡፡ --------------------------------
5. በረዶ ከመስለው እብነበረድ ላይ እየነጠረ የሚመለሰው ብርሃን ያንፀባርቃል፡፡-----------------------
6. አንቺ ድሬዳዋ ምነው ጭንቅሽ በዛ----------------------------
7. ጥቁሩ ደመና ወተት እንዳጋተ የጥገት ጡት ወደታች ተንጠልጥሏል፡፡ ----------------

## 4.3. ማጠቃለያ

ዘይቤ አንድን ሀሳብ በጥልቀት ለመግለፅ ሲታሰብ ሆን ተብሎ ከቋንቋው ስርዖት ማፈንገጥና ሀሳብን ግብ መቺ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ የሚረዳን የቋንቋ ብልሀት መሆኑን ተገልፆል፡፡ የዘይቤ አይነቶች በርካታ ቢሆንም በዚህ ክፍል የሚዘወተሩትና በብዛት በአገልግሎት ላይ የሚውሉትን በምሳሌ በማስደገፍ ቀርቦል፡፡ ዘይቤ ጥልቀት ያለው የቋንቋ አጠቃቀም በመሆኑ በንግግርም ሆነ በፅሑፍ ወቅት በመጠቀም ስታዳብሩት የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ይርባችኋል፡፡

**ማገናዘቢያ**

የክፍል አራትን ትምህርት እዚህ ላይ ጨርሳችኋል፡፡ በትምህርቱ የቀረቡትን ነጥቦች ምን ያህል እንደተገናዘባችሁ እንዳልተነገነዘባችሁ ለማረገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦላችኋል፡፡
የቀረበውን ነጥብ የምታቁት ከሆነ /✓/ ምልክት በሳጥኑ ውስጥ አስቀምጥ፡፡ ያልተረዳችሁት ካለ ተመልሳችሁ ከልሱ፡፡

- የዘይቤ ምንነትን መግለፅ እችላለሁ፡፡ ☐
- ዘይቤ ሀሳብን /መልእክትን/ አጉልቶ ማሳየቱን ተረድቻለሁ፡ ☐
- በስፋት የምንገለገልባቸውን የዘይቤ ዓይነቶች መግለፅ ችያለሁ፡፡ ☐
- በተነፃፃሪና በተለዋዋጭ ዘይቤ መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ችያለሁ፡፡ ☐
- በሰውኛና በእንቶኔ መካከል ያለውን ልዩነት መግለፅ እችላለሁ፡ ☐
- ከቀረበው ፅፍ ዘይቤን ለይቼ ለማውጣት ችያለሁ፡፡ ☐
- በንግግርም ሆነ በፅሑፈ ዘይቤን በመቀጠም ሀሳቤን ለመግለፅ ችያለሁ፡ ☐

አባሪ ሦስት፦ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ቅጽ 1

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## ድኅረምረቃ መርሐግብር
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ኮሌጅ አማርኛ (Amha 101 ) የርቀት ትምህርት ሞጁዩል የቅርጽና የይዘት አደረጃጀት በሰነድ ፍተሻ ዘዴ አማካኝነት ለመፈተሽ የተዘጋጀ መስፈርት / የመቆጣጠሪያ ቅጽ/

**1. ቅርጽን በሚመለከት የተዘጋጀ የመቆጣጠሪያ ቅጽ**

| ተ.ቁ | ዓይነት /Item/ | አዎን | በመጠኑ | አይደለም | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሞጁዩሉ ዕይታን ይስባል? | | | | |
| 2 | ይዘቱ የተጻፈባቸው ፊደሎች መጠን ለማንበብ አመቺ ነው? | | | | |
| 3 | መልስ ለመስጠትም ሆነ ማስታወሻ ለመያዝ በቂ ቦታ ተሰጥቷል? | | | | |
| 4 | ከገጽ ወደ ገጽ ከፊት ወደኋላ እንደአስፈላጊነቱ በማገናዘብ ለማንበብ የሚያግዙ መመሪያዎች ግልጽ ናቸው? | | | | |
| 5 | ከገጽ ወደ ገጽ ከፊት ወደኋላ እንደአስፈላጊነቱ በማገናዘብ ለምንበብ የሚያግዙ ምልክቶች ግልት ናቸው? | | | | |

2. የይዘት አድረጃጀትን በሚመለከት የተዘጋጀ የመቆጣጠሪያ ቅጽ ቅጽ 1

2.1. ዓላማዎችን በሚመለከት የተረዘጋጀ የመቆጣጠሪያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | በየክፍሉ/ምዕራፍ የተነደፉ ዓላማዎች | አዎን | በከፊል | አይደለም | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግልጽ ናቸው? | | | | |
| 2 | ከይዘት ጋር የተዛመዱ ናቸው? | | | | |
| 3 | አመላካች ናቸው? | | | | |
| 4 | ከተግባሮችና ከመልመጃዎች ጋር የተዛመዱ ናቸው? | | | | |
| 5 | ለመማር ያለን ፍላጎት የሚያነሳሱ ናቸው? | | | | |

2.2. ይዘትን በሚመለከት የተዘጋጀ የመቆጣጠሪያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | በየክፍሉ/ምእራፍ የቀረቡ ይዘቶች | አዎን | በከፊል | አይደለም | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቋንቋ አጠቃቀማቸው ግልጽ ነው? | | | | |
| 2 | በበቂ ሁኔታ የተብራሩ ናቸው? | | | | |
| 3 | በቂ መግለጫዎች /ምሳሌዎች/ አሏቸው? | | | | |
| 4 | በደረጃ የተደራጁ ናቸው/ ከቀላል ወደ ካባድ/? | | | | |
| 5 | ያልተጨናነቁ ናቸው/በየመጠኑ የተከፋፈሉ/? | | | | |
| 6 | በየምእራፉ ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ቀርበዋል? | | | | |



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ቅጽ 1

2.3. ተግባሮችንና መልመጃዎችን በሚመለከት የተዘጋጀ የመቆጣጠሪያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | በየክፍሉ/ምዕራፍ የቀረቡት ተግባሮችና መልመጃዎች | አዎን | በከፊል | አይደለም | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አነቃቂ ናቸው ? | | | | |
| 2 | ከአላማ ጋር የተዛመዱ ናቸው? | | | | |
| 3 | ተገቢ ማመሳከሪያ አላቸው? | | | | |
| 4 | የግል ጥረትን ያበረታታሉ? | | | | |
| 5 | ከይዘት ጋር የተዛመዱ ናቸው? | | | | |
| 6 | በአጭር ርቀት የተደራጁ ናቸው? | | | | |
| 7 | በበቂ ሁኔታ የቀረቡ ናቸው? | | | | |

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
# ድኅረ ምረቃ መርሐግብር
# የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
# የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## በርቀት ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በድብረብርሀን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለርቀት ትምህርት መርሀግብር በተዘጋጀው፤ ኮሌጀ አማርኛ የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ላይ ከርቀት ትምህርት መርሀግብር አንፃር መረጃ መሰብሰብ ነው፤ የሚሰበሰበውም መረጃ ለጥናት ተግባር ከመሆን ባሻገር ለተለየ ጉዳይ አይውልም፤ በመሆኑም እርስዎ የሚሰጡት መረጃ ለጥናቱ ውጤታማነት አስተዋፅዖ ስላለው የተዛቡትን በቀናነት እንዲያካፍሉን በትህትና እንጠይቃለን ::

በቅድሚያ ጊዜዎን ሰውተው ይህንን መጠይቅ ለመሙላት ስለተባበሩን እናመሰግናለን ::

ክፍል አንድ :- ግለሰባዊ መረጃ

*መመሪያ* :- ይህን ምልክት በሳጥኑ ውስጥ በመጻፍ ምላሽዎን ያሳዩ::

1. *ፆታ* ወ ☐ ሴ ☐
2. የትምህርት ክፍል
   - አማርኛ ☐
   - እንግሊዝኛ ☐
   - ሥነ-ውበት ☐
   - ተፈጥሮ ሳይንስ ☐
   - ኅብረተሰብ ሳይንስ ☐
3. የእገዛ ጣቢያ
   - ደ/ብርሀን ☐
   - አጣዬ ☐
   - መራኛ ☐
   - መሀልሜዳ ☐

## ክፍል ሁለት

መመሪያ :- በሳጥን ውስጥ ምላሽ ለሚፈልጉ ጥያቄዎች ይህን "X" ምልክት በመጻፍ ምላሽዎን ያሳዩ፤ ማብራሪያ ለሚፈልጉ ጥያቄዎች ግን ግልጽ ምላሽ ይስጡ::

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| 1. የሞጁዩሉ ውጫዊ ገጽታ ለመማር ያነሳሳል ? | ☐ | ☐ |
| 2. መመሪያዎችና ምልክቶች አመላካች ናቸው ? | ☐ | ☐ |
| 3. የፊደሎች መጠን ለዕይታ አመቺ መው? | ☐ | ☐ |
| 4. ማስታወሻ ለመያዝ የተሰጡ ቦታዎች በቂ ናቸው ? | ☐ | ☐ |
| 5. ለመልስ መስጫ የተተወ ቦታዎች በቂ ናቸው ? | ☐ | ☐ |
| 6. በየይዘቱ የተነደፉት ዓላማዎች | | |
| • ለመማር ያለኝን ፍላጉት ያነሳሳሉ? | ☐ | ☐ |
| • የሚጠበቅብኝን ይጠቁሙኛል? | ☐ | ☐ |
| • ከተግባሮችና መልመጃዎች ጋር ይዛመዳሉ? | ☐ | ☐ |

7. ለተራ ቁጥር ሦስት አይደለም የሚል ምላሽ ካለዎት ምክንያቱን ቢገልጹ::

---------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------

| 8. ተግባሮችና መልመጃዎች | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| • አነቃቂ ናቸው | ☐ | ☐ |
| • ከዓላማ ጋር ይዛመዳሉ | ☐ | ☐ |
| • ተገቢ ማመሳከሪያዎች አላቸው | ☐ | ☐ |
| • ፈጠራን ያበረታታሉ | ☐ | ☐ |
| • በበቂ ሁኔታ ቀርበዋል | ☐ | ☐ |
| • የግል ጥረትን ያበረታታሉ | ☐ | ☐ |
| • በመተባበር ለመማር ያስችላሉ | ☐ | ☐ |

| 9. የቀረቡ ይዘቶች | አንዳንዶቹ | ሁሉም |
|---|---|---|
| • መጨናነቅ ይታይባቸዋል | ☐ | ☐ |
| • ግልጽነት ይጎላቸዋል | ☐ | ☐ |
| • በጣም አንሰዋል/በበቂ ሁኔታ አልተብራሩም | ☐ | ☐ |

ABABA UNIVERSITY

10 በተራ ቁጥር 9 "አንዳንዶቹ" ብለው ለሰጡት መልስ ምሳሌ ቢሰጡ

---------------------------------------------------

---------------------------------------------------

11. ተጨማሪ አጋዥ መጽሐፍት የሚፈልጉ ይዘቶች ቢዘረዝሩ

---------------------------------------------------

---------------------------------------------------

---------------------------------------------------

12 በሌላ ሚዲያ ሊታገዙ የሚገባቸው ይዘቶች አሉ?

በሬዲዮ ☐ በቴሌቪዥን ☐ በቴፕ ☐ በቪዲዮ ☐

13. የተሰጡ የፕሮጀክት ጥያቄዎች

ከባድ ናቸው ☐ ተገቢ ናቸው ☐ ቀላል ናቸው ☐

ቅጽ 2

## ክፍል ሦስት

መመሪያ ፡ በሞጁዩሉ ስትማሩ ለመረዳት የሚያስቸግራችሁ ክፍሎች ሊያጋጥሟችሁ ይችላል ፡ በመሆኑም ችግርችንና ደረጃቸውን ለመለየት ይቻል ዘንድ በተራ ቁጥሮች ለተጻፉት ሐረጎች ከፊት ለፊታቸው ካሉት ረድፎች ይህን "X" ምልክት በመጠቀም ስምምነትዎን ያሳዩ፡ በደካማነት ለፈረጃቸው ግን በተሰጠው ቦታ ይዘቱን /ክፍሉን በምሳሌነት ይጠቁሙ

| ተ.ቁ. | ዓይነት /Item/ | እጅግ በጣም ጥሩ | በጣም ጥሩ | ጥሩ | ደካማ | በደካማነት የመደቡትን በምሳሌ ይጠቁሙ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የዓላማ ግልጽነት | | | | | |
| 2 | የቋንቋ ግልጽነት | | | | | |
| 3 | የይዘት ግልጽነት | | | | | |
| 4 | የልዩ ልዩ መግለጫዎች ግልጽነት | | | | | |
| 5 | የሂደት መከታተያ መልመጃዎች | | | | | |
| 6 | የማመሳከሪያ ምላሾች አመለካችነት /ተገቢነት | | | | | |

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
# ድኅረምረቃ መርሐግብር
# የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
# የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## በአዘጋጆች እና በመምህራን /በቱቶሮች/ የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በደብረብርሀን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለርቀት ትምህርት መርሐግብር በተዘጋጀው፤ ኮሌጅ አማርኛ /Amha-101 / የርቀት ትምህርት ሞጁዩል ላይ ከርቀት ትምህርት መርሐግብር አንጻር መረጃ መሰብሰብ ነው፤ የሚሰበሰበው መረጃ ለጥናት ተግባር ከመሆን ባሻገር ለተለየ ጉዳይ አይውልም፤ በመሆኑም እርስዎ የሚሰጡት መረጃ ለጥናቱ ውጤታማነት አስተዋጽኦ ስላለው የታዘቡትን በቀናነት እንዲያካፍሉን በትህትና እንጠይቃለን።

በቅድሚያ ጊዜዎን ሰውተው ይህንን መጠይቅ ለመሙላት ስለተባበሩን እናመሰግናለን።

ክፍል አንድ ፡- ግለሰባዊ መረጃ

መመሪያ ፡- ይህን "X" ምልክት በሳጥኑ ውስጥ በመጻፍ ምላሽዎን ያሳዩ።

1. ፆታ ወ ☐ ሴ ☐
2. አዘጋጅ ☐ ዕገዛ ሰጪ ☐

ክፍል ሁለት

መመሪያ ፤ በሣጥን ውስጥ ምላሽ ለሚፈልጉ ጥያቄዎች ይህን "X" ምልክት በመጻፍ ምላሽዎን ያሳዩ፤ ማብራሪያ ለሚፈልጉ ጥያቄዎች ግን ግልጽ ምላሽ ይስጡ።

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| 1. የርቀት ትምህርት ሞጁዩሉ አዘጋጃጀት ስልጠና ወስጃለሁ | ☐ | ☐ |

2. የወሰዱት የስልጠና ርዕስ
   - የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አርታኢነት ☐ ☐
   - የርቀት ትምህርት ሞጁዩል አዘገጃጀት ☐ ☐
   - የርቀት ትምህርት ፈተናና ፕሮጀክት እርማት እንዲሁም መጋቢ ሚላሽ አሰጣጥ ☐ ☐
   - የርቀት ትምህርት ዕገዛ ትምህርት አሰጣጥ ☐ ☐
   - የርቀት ትምህርት አደረጃጀት እና አስተዳደር ☐ ☐
3. የርቀት ሞጁዩል ከመደበኛው መማሪያ መጽሐፍ በተለየ መንገድ መዘጋጀት አለበት ብለው ያምናሉ ☐ ☐
4. በተራ ቁጥር 3 ምላሽዎ አዎ የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

5. የተዘጋጀው ሞጁዩል ቅርፅና የፊደል መጠን በተማሪው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው ብለው ያምናሉ?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

6. በተራ ቁጥር 5 ምላሽዎ አዎ የሚል ከሆነ ቢያብራሩ

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

7. የይዘት አደረጃጀት አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል ብለው ያምናሉ? ☐ ☐
8. በተራ ቁጥር 7 ምላሽዎ አዎ የሚል ከሆነ ምሳሌ ቢሰጡ

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

9. የተዘጋጀው ሞጁዩል ለተማሪዎች ከመሰራጨቱ በፊት
   - በአርታኢያን ታይቷል ☐ ☐
   - በተወሰኑ ታላሚዎች ላይ ሙከራ ተደርጓል ☐ ☐

ቅጽ 4

ለርቀት ትምህርት አስተባባሪዎች የተዘጋጁ የቃለ መጠይቅ መሪ ጥያቄዎች (Amha 101)

1. የርቀት ተማሪዎች ከመደበኛ ተማሪዎች በተለየ መንገድ መማር እንዳለባቸው ይታወቃል ። ለዚህ የሚሰጡት ምክንያት ምንድን ነው?
2. አጠቃላይ የመማር ማስተማሩን ሂደት አስመልክቶ ተማሪዎች አስተያየት የሚሰጡበት ስርአት አላችሁ?
3. ተማሪዎች ለእገዛ በሚሰባሰቡበት ጊዜ የመማሪያ ሞጁሎችን አስመልክቶ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?
4. በየክፍለ ትምህርቱ የሞጁዩል ጥራት መቆጣጠሪያ ስልት አለ?

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች በስም የተጠቀስኩት ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ምንጮች በሙሉ በትክክል የተጠቀሱ ስለመሆናቸው እንደ ሚከተለው በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም:- ዕዝራ አየለ ቱሣ

ፊርማ: ----------------

አድራሻ:- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋችና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ::

የማስረከቢያ ቀን:- 13/10/2000 ዓ.ም